# የክርስቶስ ወንጌል

J.C. Choate

WORLD EVANGELISM PUBLICATIONS
Winona, MS

© Copyright, World Evangelism Publications

This printing - 5,000 copies - 2023 – **Amharic**

**InDesign Layout**: Shane Fisher

**Translated by**: Belay Kebede Areri
**WhatsApp number**: 0913611000
**Email**: ddcoc321@yahoo.co.uk

**Websites**:
www.worldevangelismlibrary.org
www.gospelgazette.com
www.worldevangelism.org
www.worldevangelismmedia.com

Macaafa Kana Kaffaltii malee kan Argattan.
Waldaa Kristoos Dirree Dawa, Lakkoofsa saanduqa Poostaa 1376,
lakkoofsa bilbilaa 0913611000.

ማሳሰቢያ ለተማሪዎቻችን፦ ይህ የመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርት የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ንብረት ነው። ለዚህ ትምህርት ምንም ዓይነት ክፍያ አናስከፍልም፣ ትምህርቱን አጥንታችሁ መልሶቻችሁን በራሳችሁ ነጭ ወረቀት ላይ በመሙላት መልስ መስጫችሁንና መፅሐፉን እንድትመልሱልን እንጠይቃችዋለን፣ የምትልኩበት አድራሻ ለወንጌላዊ በላይ ከበደ ፖስታ ሣጥን ቁጥር 1376 ድሬ ዳዋ ስልክ ቁጥር 0913611000 እሜይል ddcoc321@yahoo.co.uk ብላችሁ ላኩልን። የናንተንም አድራሻ በመልስ ምስጫ ወረቀታችሁ ላይ ማስፈርን አይዘንጉ። እናመሰግናለን ጌታ ይባርካችሁ

**NOT FOR SALE**

**Printed by**:
World Evangelism Publications
Winona, MS 38967

# ማውጫ


ትምህርት አንድ______የክርስቶስ ወንጌል........................................4
ትምህርት ሁለት˙˙_______የወንጌል እውነታዎች...................................7
ትምህርት ሦስት____________የወንጌል ጥሪ.................................10
ትምህርት አራት____________ለወንጌል መታዘዝ..............................14
ትምህርት አምሥት___________ወንጌልን መስማት..............................17
ትምህርት ስድስት__________በእግዚአብሄር ማመን.............................21
ትምህርት ሰባት___________የታጥያት ንሠሐ...................................25
ትምህርት ስምንት____________ክርስቶስን መመስከር...........................28
ትምህርት ዘጠኝ___________ለታጥያት ሥርየት መጠመቅ.......................31
ትምህርት አሥር____________የወንጌል በረከቶች.................................35
ትምህርት አሥራ አንድ_________ወንጌልን መስበክ................................39
ትምህርት አሥራ ሁለት________ሌላ ወንጌልን መስበክ..........................43
ትምህርት አሥራ ሦስት________ወንጌልን ማደናቀፍ..............................47

# ትምህርት አንድ
# የክርስቶስ ወንጌል

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የክርስቶስን ወጌል ብዙ ጊዜ እናነባለን። ሌሎች ሲናገሩ እንሰማለን። ብዙ ጊዜ ወጌልን በተለያዩ መንገዶች እንጠቀሳለን። ግን ወንጌል ምንድነው? የክርስቶስ ወንጌል ምንድነው? ለመልሶቹን ለማግኘት ወደ ቅዱሳት መፅሐፍት እንሂድ። ጳውሎስ ሲፅፍ እንዲህ ይላል “መፅሐፍ በእሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም ይላልና በአይሁዳዊና በግሪክ ሰው መካከል ልዩነት የለምና አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና ለሚጠሩትም ሁሉ ባለጠ ነው። የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙጽ እንዴት ያምናሉ? የለሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ? መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደተፃፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ?” (ሮሜ 10፡11~15) በመሰረቱ እንግዲህ ወንጌል የሚለው ቃል የምሥራች የማዳን፣ የእውነት ቃል፣ ተስፋ ኪዳን ማለት ነው። የክርስቶስን ምሥራች በተመለከተ ከሌሎች ዜናዎች ሁሉ የተለየ ነው።

ይህ የምሥራች ወይም መልካም ዜና የተመሰረተው በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት፣ መቀበር እና ትንሳኤ ላይ ነው። ሐዋሪያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሲፅፍ እንዲህ ይላል “ወንድሞች ሆይ የሰበኩላችሁን ደግሞም የተቀበላችሁትን በእርሱም ደግሞ የቆማችሁበትን በእርሱም ደግም የምትድኑበትን ወንጌል አሳስባችዋለሁ። በከንቱ ካላመናችሁ በቀር ብታስቡት በምን ቃል እንደሰበኩላችሁ አሳስባችዋለሁ እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ እንዲህ ብዬ መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለኃጥያታችን ሞተ ተቀበረም መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ” (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡1~4) ግን ይህ እንዴት መልካም ዜና ሊሆን ይችላል? ምክንያቱም አንድ ሰው የሚድነው እና የዘላለም ህይወት ጽፋ ያለው በክርስቶስ ሞት መቀበርና ትንሳኤ ነው። ይሄው ጸሐፊ እንደገና “በወንጌል አላፍርምና አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሄር ኃይል ለማዳን ነውና” (ሮሜ 1፡16) ይላል።

ሁላችንም በዕለት ተዕለት ህይወታችን ምሥራች ምን ማለት እንደሆነ እናውቃለን። አንዳንድ በረከቶች በመንገዳችን ሲመጡ በጣም ደስተኞች ነን እናም ታሪኩን ለሁሉም ሰው ማካፈል እንፈልጋለን። ይህ ተፈጥሯዊ ብቻ ነው። በክርስቶስ በኩል በሚመጣው የምሥራች የመዳን ዜና መስማት ደግሞ እጅግ አስደናቂ ነው። እውነትም ነው። ጌታን ከታዘዝንና በፀጋው ከዳንን እንግዲያውስ ስለእርሱ ለዓለም መንገር አለብን ክርስቶስ የተናገረው ይህን ነው “እንዲህም አላቸው ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ያመነ የተጠመቀም ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል” አላቸው (ማርቆስ 16፡15~16)

ቅዱሳት መጽሐፍትም ስለ እግዚአብሄር ወንጌል ይናገራሉ። ጳውሎስ ያለውን ስናነብ “ሐዋሪያ ሊሆን የተጠራ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ጳውሎስ በነቢያቱ አፍ በቅዱሳን መጻህፍት አስቀድሞ ተስፋ ለሰጠው ለእግዚአብሄር ወንጌል

ተለየ። ይህም ወንጌል በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለተወለደ እንድቅድስና መንፈስ ግን ከሙታን መነሣት የተነሣ በኃይል የእግዚአብሄር ልጅ ሆኖ ስለ ተገለጠ ስለ ልጁ ነው። እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በእርሱም ስለ ስሙ በአህዛብ ሁሉ መካከል ከእምነት የሚነሣ መታዘዝ እንዲገኝ ጸጋንና ሐዋሪያትን ተቀበልን በነርሱም መካከል የኢየሱስ ክርስቶስ ልትሆኑ የተጠራችሁ እናንተ ደግሞ ናችሁ በእግዚአብሄር ለተወደዳችሁና ቅዱሳን ልትሆኑ ለተጠራችሁ በሮሜ ላላችሁት ሁሉ ከእግዚአብሄር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሠላም ለእናንተ ይሁን" (ሮሜ 1፡1~7) በተመሣይ መልኩ ጸሐፊው ቀጥሎ ስለ እግዚአብሄር ወንጌል ይናገራል "ነገር ግን ሩጫዬንና ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልኩትን አገልግሎት እርሱም የእግዚአብሄርን ጸጋ ወንጌልን መመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደከንቱ ነገር እቆጥራለሁ" (የሐዋሪያት ሥራ 20፡24) ይህ ገፅ በእግዚአብሄርና በክርስቶስ መካከል ያለውን አንድነት ብቻ ያሳያል። ወንጌልን ለዓለም እንዲሰጥ ክርስቶስን የላከው እግዚአብሄር ነው። በዚህ መንገድ ወይ የእግዚአብሄር ወንጌል ወይ የክርስቶስ ወንጌል ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

ዳግመኛም ስለ ከበረው ወንጌል እናነባለን፣ ስማው " የብሩክ እግዚአብሄርንም ክብር እንደሚገልጥ ለእኔ አደራ ተሰጠኝ ወንጌል የሆነውን ደህና ትምህርት" (1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡11) እንደገናም "ወንጌላችን የተከደነ ቢሆን እንኳ የተከደነባቸው ለሚጠፉ ነው። ለእነርሱም  የእግዚአብሄር ምሣሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ። ወንጌል የከበረ ነው ተብሏል። ትርጕሙም ሰማያዊ ዘላለማዊ ወዘተ ማለት ከእግዚአብሄርና ከክርስቶስ ነውና።

በማቴዎስ፣ በማርቆስ፣ በሉቃስ እና በዮሐንስ "የመንግስቱ ወንጌል" የሚለው አገላለፅ ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል። "ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ የመንግስትም ወንጌል እየሰበከ በህዝብም ያልውን ደዌና ሕማም እየፈወሰ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዞር ነበር" (ማቴዎስ 9፡35)  "ዮሐንስም አልፎ ከተሰጠ ቦኃላ አየሱስ የእግዚአብሄርን መንግስት ወንጌል እየሰበከና ዘመኑ ተፈጸመ የእግዚአብሄርም መንግስት ቀርባለች ንሰሃ ግቡ በወንጌልም እመኑ እያለ ወደ ገሊላ መጣ" (ማርቆስ 1፡14~15)። በዚህ ወቅት ክርስቶስና ሌሎች የመጪውን መንግሥት ምሥራች ስብከዋል። በሌላ አነጋገር ገና አልተመሰረተም ነበር ግን በቅርቡ ይሆናል። ቦኃላም በጌታ ሞት መቀበርና በክርስቶስ ትንሳኤ ላይ ተመስረተው በእውነት ወንጌል ተሰበከ ትዕዛዙንም የሚታዘዙ ድነው ወደ ጌታ ቤተክርስቲያን ወይም ወደ መንግሥቱ ተጨመሩ (የሐዋሪያት ሥራ 2)

ለኤፌሶን ክርስቲያኖች ሲናገር የመዳንን ወንጌል እናነባለን ሐዋሪያው እንዲህ ይላል  "እናንተም ድግሞ የእዉነትን ቃል ይሄውም የመዳናችሁን ወንጌል ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስአምናችሁ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ" (ኤፌሶን 1፡13) እንግዲህ መዳን የሚያመጣው ወንጌል ነው። አንዳንድ ጊዜ የምንናገረው ስለ ድነት የወንጌል እቅድ ነው። እሱም የጌታን እቅድ

ወይም ሰውን የማዳን መንገድ ለመግለጽ ብቻ ነው።
ቀጥለን ወደ ሮሜ ሰዎች 10፡15 ስንመለስ የሰላም ወንጌል የሚለውን እናገኛለን ፀሐፊው "መልካሙን የምስራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደተጻፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ" (ሮሜ 10፡15) "እንግዲህ ወገባችሁን ታጥቃችሁ የፅድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ። በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፊላፃዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነት ጋሻ አንሡ" (ኤፌሶን 6፡14~16) ወንጌል ሠላምን ያመጣ የአዕምሮ ሠላም የነፍስ ሠላም ከባለንጀሮቻችን ጋር ሠላም። ክርስቶስ የሠላም ሰው ነበረ እና ወንጌሉ የሱን ሠላም ያመጣል። ከእግዚአብሄር ጋር ሠላም። በእርግጥም ይሄ ነው መልካም ዜና። በመጨረሻም የተስፋ ወንጌል እንደሆነም ተነግሮናል "እናንተም ነውርና ነቀፋ የሌላችሁና ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ያቀርባችሁ ዘንድ በፊት የተለያችሁትን ክፉ ሥራችሁንም በማድረግ በአሳባችሁ ጠላቶች የነበራችሁትን አሁን በሥጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ። ይህም ተመሥርታችሁና ተደላድላችሁ ከሰማችሁትም ከወንጌል ተስፋ ሳትናወጡ በሃይማኖት ፀንታችሁ ብትኖሩ ይሆናል። ያም ወንጌል ከሰማይ በታች ባለው ፍጥረት ሁሉ ዘንድ የተሰበከ ነው። እኔም ጳውሎስ የእርሱ አገልጋይ ሆንሁ" (ቆላሲያስ 1፡21~23) ወንጌልን በመታዘዝ ምክንያት አንድ ሰው የመኖር የዘላለም ህይወት ተስፋ ይኖረዋል። ፀሐፊው ስለዚህ እየተናገረ ነው። ተስፋ ከወንጌል ውጪ በሌላ መንገድ አይመጣም።

ከጊዜ ወደ ጊዜ ጳውሎስ ሲናገር "ወንጌሌ" ወይም "ወንጌላችን" ይላል። ይህ ምን ማለት ነው? እሱ እና ሌሎች የተቀበሉትን ወንጌል እና ጌታ ለሌሎች እንዲሰብኩ የሰጣቸውን ወንጌል ለማመልከት ብቻ ነው። በዚህ ረገድ እንዲህ ይላል "ወንጌላችን በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙ መረዳትም እንጂ በቃል ብቻ ወደ እናንተ አልመጣምና በእናንተ ዘንድ ስለ እናንተ እንዴት እንደነበርን ታውቃላችሁ" (1ኛ ተሰሎንቄ 1፡5) እዚህ ላይ እንደተገለፀው እና በሮሜ 1፡16 እንደሚለው ወንጌሉ የሚያምኑትንና የሚታዘዙትን የሚያድን በመሆኑ ኃይለኛ ነው።

እንግዲህ ይህ በቅዱሳት መጻህፍት ቃል ውስጥ ያለው ወንጌል ነው። ኃይለኛ ነው። ዛሬም አዲስ የማያረጅ እንደክርስቶስ ነው። ያድናል። ተስፋን ይሰጣል ለሁሉም ሊሰበክ የሚገባው ብቸኛው የማዳን ኃይል ወንጌል ነው። ከእግዚአብሄርና ከክርስቶስ የወጣ ነው የከበረ ነው፣ ይባርካል ይሞግታል መፈታትን ያመጣል። እሱ አንድ ነው ለሁሉም ነው። ይህ በእውነት መልካም ዜና ነው።

## ጥያቄዎች

1. ሮሜ 10፡11~15 አንብብ
2. ወንጌልን ግለፅ
3. ወንጌል በምን ላይ የተመሰረተ ነው?
4. እንዴት ነው የክርስቶስ ሞት፣ መቀበር እና ትንሳኤ መልካም ዜና ሊሆን

የሚችለው?

5. ሮሜ 1፡16~17 ጥቀስ
6. በዓለማዊ ጉዳዮች ውስጥ ለምሥራች ምላሽ የምንሰጠው እንዴት ነው?
7. ክርስቶስ በማርቆስ 16፡15~16 ምንን አስተማረ?
8. ወንጌል የእግዚአብሄር ነው ብለን በምን መንገድ መናገር እንችላለን?
9. ወንጌል እንዴት ክቡር እንደሆነ አስረዳ
10. “የመንግሥት ወንጌል” በሚለው ላይ ተወያዩ
11. ይህንን የሚደግፍ የተወሰነ ጥቅስ ስጥ
12. ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጌል የተሰበከው መቼ ነው?
13. ድነትን የሚያመጣው ምንድነው? እንዴት?
14. ወንጌል በምን መንገድ ነው ሠላምን የሚያመጣው?
15. ተስፋችን በምን ላይ ነው?
16. ጳውሎስ “የኔ ወንጌል”ወይም “ወንጌላችን” የሚለው ለምንድነው?
17. ምን ያህል ኃይል አለው?
18. ስንት ወንጌል ነው ያለው?

## ትምህርት ሁለት
## የወንጌል እውነታዎች

ቅዱሳት መጻሕፍት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሞተ፣እንደተቀበረ እና ከዚያም ከመቃብር እንደተነሣ በግልፅ ያስተምራሉ፡፡ በኢየሱስ ታሪክ ውስጥ ያሉት እነዚህ ክስተቶች የወንጌል እውነታዎች ተብለው ተጠቅሰዋል፡፡ ጳውሎስ እያንዳንዳቸውን ጠቅሶ ለቆሮንቶስ ወንድሞቸሁ በጻፈው የመዳናቸውን ከእነዚህ እውነታዎች ጋር ያለውን ግንኙነት በማሳየት ነው፡፡ “ወንድሞች ሆይ የሰበኩላችሁን ደግሞም የተቀበላችሁትን በእርሱም ደግሞ የቆማችሁበትን በእርሱም ደግሞ የምትድኑበትን ወንጌል አሳስባችዋለሁ፡፡ በከንቱ ካላመናችሁ በቀር ብታስቡት በምን ቃል እንደሰበኩላችሁ አሳስባችዋለሁ፣ እኔ ድግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ እንዲህ ብዬ መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጥያታችን ሞተ ተቀበረም መጽሐፍ እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ” (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡1~4) በሌላ አነጋገር የክርስቶስ ወንጌል በእነዚህ እውነቶች ላይ ያረፈ ነው፡፡ ክርስቶስ ባይሞት ባይቀበር ከመቃብርም ባይነሣ ያኔ ወንጌል አይኖርም ነበር፡፡ ስለዚህ መዳን የለም፡፡ ነገር ግን እርሱ እንደሞተ ከተቀበረ እና ከመቃብር ከተነሣ ቦኃላ ለወንጌል መሰረት አለን ስለዚህም ዓለምን ለውጦታል፡፡

አሁን ለአንተ እና ለእኔ ምን እንደያዙ ለማየት የወንጌልን እውነታዎች አንድ በአንድ ለማየት እንሞክራለን

1. የክርስቶስ ሞት

መጽሐፍ ቅዱስ ደጋግሞ የክርስቶስን ሞት ይናገራል፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሄርን

ቃል እራሱን አድምጥ “በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን፡፡ እርሱ በእግዚአብሄር መክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሄር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በስውም ምሣሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፡፡ በምሥሉም እንደሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ ለሞትም ይሄውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ” (ፊልጵስዩስ 2፡5~8) “ነገር ግን በእግዚአብሄር ጸጋ ስለሰው ሁሉ ሞትን ይቀምስ ዘንድ ከመላእክት ይልቅ በጥቂት አንሶ የነበረውን ኢየሱስን ከሞት መከራ የተነሣ የክብርና የምስጋናን ዘውድ ተጭኖ እናየዋለን” (ዕብራዊያን 2፡9)

ክርስቶስ ለማን ነው የሞተው? በዕብራዊያን 2፡9 ላይ እንዳየነው ለሰው ልጅ በሙሉ ነው የሞተው፡፡ ቅዱሳት መፅሐፍት እንደሚነግሩን ለኃጥያተኞች ነው የሞተው “ነገር ግን ገና ኃጥያተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሄር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል” (ሮሜ 5፡8) ግን ለምን ለኃጥያተኞች ሞተ? ደህንነት እና ተስፋ ሊሰጥ፡፡ እንዲህ እናነባለን “ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሄር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ነው” (1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡4)፣ “ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፣ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንሰሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፉ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሳል” (2ኛ ጴጥሮስ 3፡9)

ያም ማለት አንድ ሰው ለእኔ እና ለአንተ ሞተ ማለት ነው፡፡ እስቲ አስበው፡፡ እኛ ኃጥያተኞች ብንሆንም የእግዚአብሄር ጠላቶች ብንሆንም ለእንዲህ ዓይነቱ ጸጋና ምህረት የማይገባን ብንሆንም ክርስቶስ ከሰማይ ወጥቶ ወደዚህች የኃጥያት ምድር ሊመጣ ፈቃደኛ ነበረ፡፡ እናም እንድንበትና የዘላለም ህይወት ተስፋ እንዲኖረን ሀዘን እና በመስቀል ላይ መሞት (ሮሜ 5፡6~7) እንዴት ድንቅ ነው ! ግን አስቡት፣ እሱ እንዲሁ ለዓለም ሁሉ ሞቷል፡፡ ትናንት ዛሬ እና ነገ፡፡ ምንኛ አመስጋኞች መሆን ይገባናል፣ ይህ ደግሞ ለእሱ ያለንን ታዛዥነትንና ታማኝነትን ያስገኝልናል፡፡ ከዚህ ያነሰ ለማድረግ እንዴት እንደፍራለን?

2. የክርስቶስ መቀበር

ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከሞተ ቦኃላ ዘገባው የሚለው “በመሸም ጊዜ ዮሴፍ የተባለው ባለጠጋ ሰው ከአርማትያስ መጣ እርሱም ደግሞ የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ነበረ፡፡ ይሄውም ወደ ጲላጦስ ቀርቦ የኢየሱስን ሥጋ ለመነው ጲላጦስም እንዲሰጡት አዘዘ፡፡ ዮሴፍም ሥጋውን ይዞ በንፁህ በፍታ ከፈነው፡፡ ከዓለት በወቀረው በአዲሱ መቃብርም አኖረው በመቃብሩም ደጃፍ ታላቅ ድንጋይ አንከባሎ ሄደ፡፡ መግደላዊት ማርያምም ሁለተኛይቱም ማርያም በመቃብሩ አንጻር ተቀምጠው በዚያ ነበሩ” ((ማቴዎስ 27፡57~61)

አሁን በብዙ መልኩ በጌታ መቀበር ላይ በተለይም ለዚያ ጊዜ የተለየ ወይም ያልተለመደ ነበር፡፡ ሰዎች በየቀኑ ይሞታሉ ይቀበራሉ ይህ በዓለም ሁሉ እውነት ነው እና ከፍጥረት ጀምሮ እውነት ነው፡፡ ነገር ግን ጌታ ሞቶ ቢቀበርም ዳግመኛ

እንደሚነሣ ሆነ እንዲህ ብሎም አውጇል “ ኢየሱስም መልሶ ፦ ይህን ቤተመቅደስ አፍርሱት በሦስተኛው ቀን አነሣዋለሁ አላቸው” (ዮሐንስ 2፡19) በእርግጥ በዚያን ሠዓት ምን ለማለት እንደፈለገ አልተረዱም ነገር ግን ቢረዱት ኖሮ ያምኑት ነበር? ከሞቱ እና ከመቀበሩ በኃላ ምን ተከሰተ? ደቀመዛሙርቱ ሁሉም ነገር እንደጠፋ ተሰማቸው፡፡ በድንጋጤ ውስጥ የገቡ ይመስላሉ፡፡ ታዲያ ምን ሆነ? ኢየሱስ እንደሚመጣ ቃል በገባ መሰረት መጣ፡፡

3. የክርስቶስ ትንሳኤ

ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞቶ ከዚያም በመቃብር ውስጥ ቢቀር ዓለም እርሱን እንደአስመሳይ ታስበው ይሆናል፡፡ ሞቶ በመቃብር ውስጥ ቢቀር ኖሮ ከማንም በላይ አይደለም ማለት ይቻል ነበር፡፡ ኢየሱስ ግን ከዚህ የተለየ ነው፡፡ የእግዚአብሄር ልጅ ነው፡፡ ከመቃብር እነሳለሁ አለና አደረገም፡፡ (ማቴዎስ 28) እንግዲህ ውጤቱ በትንሳኤው ምክንያት መዳን አለ፡፡ ሁሉም እንደሚነሱ ማረጋገጫ እና የዘላለም ህይወት ተስፋ አለ፡፡

ወደ ፊት ከመሄዳችን በፊት ግን ስለጌታ ትንሳኤ የሚናገሩትን አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን እናስተውል “ይህም ወንጌል በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለተወለደ እንደቅድስና መንፈስ ግን ከሙታን መነሣት የተነሣ በኃይል የእግዚአብሄር ልጅ ሆኖ ስለተገለጠ ስለ ልጁ ነው እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው” (ሮሜ 1፡4) “እርሱንና የትንሳኤውን ኃይል እንዳውቅ በመከራውም እንድካፈል ወደ ሙታንም ትንሳኤ ልደርስ ቢሆንልኝ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ” (ፊልጵስዩስ 3፡10) “ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሳቱ ለህያው ተስፋና ለማይጠፋ እድፈትም ለሌለበት ለማያልፍም ርስት እንደምህረቱ ብዛት ሁለተኛ የወለደን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ” (1ኛ ጴጥሮስ 1፡3) “ይህም ውሃ ድግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል የሰውነትን እድፍ ማስወገድ አይደለም፡፡ ለእግዚአብሄር የበጎ ሕሊና ልመና ነው እንጂ፡፡ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ነው” (1ኛ ጴጥሮስ 3፡21) “ክርስቶስ ከሙታን ተነስቶ ወደ ፊት እንዳይሞት ሞትም ወደ ፊት እንዳይገዛው እናውቃለንና” (ሮሜ 6፡9) “ስለዚህም ነገር ሙታንንም ህያዋንንም ይገዛ ዘንድ ክርስቶስ ሞቶአልና ህያውም ሆኗልና” (ሮሜ 14፡9)፡፡

ክርስቶስ ሞቶ ተቀበረ ከመቃብርም ተነስቶአልና አሁን ጌታችንና መድኃኒታችን ነው፡፡ በእግዚአብሄር ቀኝ ነግሶአል፡፡ (ሐዋሪያት ሥራ 2) አንድ ቀንም ተመልሶ እንደሚመጣ ቃል ገብቶአል ይመጣልም (ዮሐንስ 14፡1~3) ሰዎቹ የኃጥያት ሥርየት እንዲሆንላቸው ከክርስቶስ ሞት ጋር ደሙ ፈሠሠ፡፡ (ማቴዎስ 26፡28፣ ኤፌሶን 1፡7)፡፡ አንድ ሰው ለክርስቶስ ወንጌል በመታዘዝ ነው ከደሙ ጋር የሚገናኘው እናም ኃጥያቱ የሚደመሰሰው፡፡ (ሐዋሪያት ሥራ 2፡38፣ ሐዋርያት ሥራ 22፡16) በሚቀጥሉት ትምህርቶቹ ውስጥ ይህ እንዴት እንደሚደረግ በግልፅ እንመለከታለን፡፡

ዛሬ በህይወት ያለውየጌታ ትንሳኤ ውጤት መሆኑን እርግጠኛ ይሁኑ። እንደ ታዛዥ ተከታዮቹ እኛም እንኖራለን እንነግሣለን እና ከእርሱ ጋር ለዘላለም እንኖራለን።

## ጥያቄዎች

1. ስለ ኢየሱስ መጽሐፍ ቅዱስ በግልፅ የሚያስተምረው ምንድነው?
2. የወንጌል እውነታዎችን ግለጻቸው
3. እውነታዎቹ ለምን እንደዚያ ይጠቀሳሉ?
4. 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡1~4 አንብብ
5. የክርስቶስ ወንጌልን ምንነት አብራራ
6. የኢየሱስን ሞት የሚናገሩ የተወስኑ ጥቅሶችን ስጥ
7. ክርስቶስ ለምን ነው የሞተው?
8. ለምንድነው ክርስቶስ ለኃጥያተኞች የሞተው?
9. የክርስቶስ መሞት ለእያንዳንዳችን ምን ማለት እንደሆነ ተውያዩ
10. የጌታን መቃብር ታሪክ ተናገር
11. ክርስቶስ ከሞተ እና ከተቀበረ ቦኋላ ምን አድረጋለሁ ብሎ ቃል ገባ?
12. ደቀመዛሙርቶቹ የሱን ቃል ተርድተዋል?
13. የጌታ ሞትና መቀበር ከሌሎች ሰዎች ሞትና መቀበር የሚለየው በምንድነው?
14. የክርስቶስ ትንሳኤ ውጤት ምን አመጣ?
15. የጌታን ትንሳኤ የሚናገር የተወሰነ ጥቅስ ስጥ
16. ክርስቶስ ለእኛ ምናችን ነው?
17. በአሁኑ ሰዓት ዬት ነው ያለው?
18. እንደገና ይመጣል? ከሆነ መቼ?
19. ስለ ክርስቶስ ደም አስፈላጊነት በግልፅ ተወያዩ

## ትምህርት ሦስት
## የወንጌል ጥሪ

በሐይማኖታዊው ዓለም ዛሬ እግዚአብሄር አንድን ሰው እንዴት ወደ መዳን እንደሚጠራው ብዙ የተለያዩ ሀሳቦች አሉ። አንዳንዶቹን ዋና ዋናዎቹን እንጠቅሳለን። በመጀመሪያ እግዚአብሄር በትንሽ ድምፅ እንደሚናገራቸው የሚያስተምሩ አሉ። በሁለተኛ ሌሎች ደግሞ ክርስቶስ በህልም ወይም በራዕይ ወደ እነርሱ እንደሚመጣ ይናገራሉ። ሦስተኛ ደግሞ ጌታ በተለየ ልምምድ እንደጠራቸው የሚያምኑ አሉ። በነዚህ በሦስቱም መንገዶች እነርሱን ለማዳን ወይም ለመታደግ በዚህ መንገድ በተለየ መልዕክት እንደ እንዳገኙ ያስተምራሉ። ይህ ለእኛ ማስጠንቀቂያ ነው። ምክንያቱም ሁልጊዜ እነዚህን ሰማን ወይም አየን የሚሉት ሰዎች ሲያጋጥሙን ተጠራጣሪ መሆን ስላለብን።

በመጀመሪያ ማወቅ የምንፈልገው ይህንን ነው። እግዚአብሄር ዛሬ ይናገራል ? ከተናገረስ እንዴት ይናገራል? ለሚለው ወደ ዕብራዊያን መጽሐፍ እንሂድ “ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሄር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተነግሮ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን” (ዕብራዊያን 1፡1~2) ስለዚህ ዛሬም እግዚአብሄር ይናገራል የሚናገረውም በልጁ በኩል ነው። ይህ ደግሞ በማቴዎስ 17፡5 ላይ በክርቶስ ተአምራዊ ለውጥ ላ ተናግሯል። እግዚአብሄርን አድምጥ እንዲህ ይላል “በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት” አለ

የሚቀጥለው ጥያቄ እግዚአብሄር ዛሬ ለሰው ይናገራል ወይንስ በክርስቶስ በቀጥታ ይናገራል? እነዚህን ጥቅሶች ስናነብ ይህ ይገባናል “ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያለተጻፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀመዛሙርቱ ፊት አደረገ፣ ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ አምናችሁም በስሙ ህይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጻፈ” (ዮሐንስ 20፡30~31)። እነዚህ ነገሮች ለምን ተጻፉ? ምክንያቱም እንድናምን። ግን ዬት ነ እነዚህ የተጻፉት ? በአዲስ ኪዳን ውስጥ። ስለዚህ ይህንን ካነበብን የያዙትን እውነት ካጠናን የጌታን ፈቃድ እናውቃለን ማለት ነው።

እንደገና የምናነበው “ እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሄር ቃል ነው” (ሮሜ 10፡17) ጥያቄ ፦ እምነት ከተጽፈው ውጪ በሌላ መንገድ ይመጣል? በሌላ መንገድ ቢመጣ ኖሮ መጽሐፍ ባላለ ነበር። በርግጥ ብዙዎች ይህንን ሰማን ያንን አየን በንደዚህ ዓይነት ተገለጠልን ወዘተ የሚሉ አሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ያለው አንድም ነገር የለም። ይልቁንስ ያለው እምነት ከመስማት ነው መስማትም የእግዚአብሄር ቃል ነው ነው ያለው። ስለዚህ ያለው አንድ መጽሐፍ ነው ያለው እምነትም አንድ ነው (ኤፌሶን 4፡5)

ምክንያቱም እምነት ከመስማት ስለሚመጣ መስማትም የእግዚአብሄር ቃል ስለሆነ የእጋዚአብሄር ቃል የማጥናት ጠቃሚነትን ያስተምረናል (2 ጢሞቴዎስ 2፡15) መጽሐፍ ቅዱስን መመርመር (ዮሐንስ 5፡39) ወዘተ ለነገሩ ለዚያም ነው በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ብዙ ትኩረት የተደረገው የእርሱን ሁሉን ቻይነት የሚያመለክት (2 ጢሞቴዎስ 3፡16~17)

ከዚያም ወንጌል በሸክላ ዕቃ ውስጥ እንደተቀመጠ ቅዱሳት መጻሕፍት ይነግሩናል እስቲ ጳውሎስን አድምጥ “ ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታ እንደሆነ እንጂ ራሳችንን አንሰብክምና ስለ ኢየሱስም ራሳችንን ለእናንተ ባሪያዎች እናደርጋለን። በክርስቶስ ፊት የእግዚአብሄርን የክብሩን እውቀት ብርሀን እንዲሰጥ በልባችን የበራ በጨለማ ብርሃን ይብራ ያለ እግዚአብሄር ነው። ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሄር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን” (2ኛ ቆሮንቶስ 4፡5~7)። አሁን እዚህ ጋ ምን እያለ ነው? እንዲያው ጌታ ሰዎችን እንደጳውሎስ ያሉ ግለሰቦችን ወንጌን ለወገኖቻቸው እንዲወስዱ መርጧል እያለ ነው። በሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ስለተለያዩ የእምነት ጉዳዮች

አሁን አስብ። ጌታ ለአንድ ግለሰብ ለመዳን ምን ማድረግ እንዳለበት የተናገረበትን አንድ ምሣሌ ስጥ። አትችልም። ለምሣሌ በሐዋሪያት ሥራ 8 ላይ የጌታ መልአክ ለጃንደረባው ክርስቶስን እንዲሰብክ ፊሊጶስን ላከው። ጥያቄ መልአኩ ሄዶ ፊሊጶስን በሰማሪያ ትቶት ለነበረው ሕዝብ መስበኩን ያልቀጠለው ለምንድነው? ጌታ ወንጌልን በሸክላ ዕቃ ውስጥ ስላስቀመጠ  እና የሰው ልጅ የውንጌል መልእክት እንዲያስተላልፍ ስለፈለገ ነው። እንደገናም የሐዋሪያ ሥራ 9 ላይ ሳኦል ለመዳን ምን ማድረግ እንዳለበት ጌታን ጠየቀው እናም ጌታ ዬት ማን ጋ መሄድ እንዳለበት ነገረው ቦታላም ሐናኒያ ሁሉን ነገረው (ሐዋሪያት ሥራ 22፡16) ጥያቄ ጌታ ለምን ራሱ አልነገረውም? ምክንያቱም ይህን ማድረግ ፈቃዱ አልነበረም። በሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ካሉ ሌሎች የመለወጥ ጉዳዮችም እንዲሁ ነው። ለዚህም ጌታ ዛሬ ሰዎችን ከቅዱሳት መጻሕፍት ውጪ በቀጥታ እየተናገረ እንዳልሆነ ወይም እንዲድኑ ምን ማድረግ እንዳለባቸው እየነገራቸው እንዳልሆነ የምናውቅበት ምክንያት ይህ ነው። ጌታ እዚህ ቢኖር እንኳን ለአንድ ሰው ምን ማድረግ እንዳለበት ሊነግረው አይችልም።  ሰው እንዲያደርግ ያዘዘውን ሊፈጽም ሰውዬው ራሱ ነው። ጌታ በሱ ድርሻ ገብቶ ምንም አያደርግም (ማርቆስ 16፡15~16) በሌላ አነጋገር ሰው ሊያደርግ የሚችለውን ጌታ አያደርግለትም።

ምክንያቱም ወንጌል ምድር ላይ ባለው የሸክላ ዕቃ ውስጥ ተቀምጧል፣ ለዚህም ነው ወንጌላዊያኖች ወንጌልን ይዘው መውጣት አሰፈላጊ የሆነበጥ ክርስቶስም እንዲህ ነው ያለው “ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ያመነ የተጠመቀም ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል” አላቸው (ማርቆስ 16፡15~16) እንደገና የምናነበው “የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ? መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደተጻፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ? “ (ሮሜ 10፡13~15)፣ ከዚያ መጨረሻ ላይ “ቃሉን  ስበክ በጊዜውም ያለጊዜውም ጽና ፈጽመህ እየታገስህና እያስተማርህ ዝለፍና ገሥፅ ምከርም” (2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡2)  እንግዲህ ጌታ ፈቃዱን በዚህ መልኩ ሊገልጥ  እንደመረጠ ታያለህ  እና ይህን ለመረዳት ቀላል ነው።

እውነት መሆኑን ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች ጽፏል “ለዚህም የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ለማግኘት በወንጌላችን ጠራቸሁ” ይላል (2ኛ ተሰሎንቄ 2፡14) ጳውሎስ ምን ማለቱ ነው? ጳውሎስ ጌታ የተሰሎንቄን ሰዎች በወንጌል እንደጠራ ይናገራል። ይህም ጳውሎስ ወንጌልን ሰበከላቸው ሰምተውም ታዘዙት ስለዚህም ወደ ክርስቶስ በዚህ መንገድ ተጠርተዋል። ሌላው የማስቀመጫ መንገድ ክርስቶስ በወንጌል ስብከት ወደ መዳን አመጣቸው።

አሁን በዛሬው ጊዜስ ? እንዴት ተጠርተናል? እኛም ክርስቲያኖች የሆንን በተመሳሳይ በወንጌል ተጠርተናል። ይህም ወንጌል ተሰብኮልናል። ሰምተናል። አምነናል ታዘናል እና ጌታ አዳነን። ጌታ አንድን ሰው በአንድ መንገድ ሌላውን በሌላ

መንገድ አይጠራም ይልቁንም በአንድ ወንጌል ብቻ ነው የሚጠራው።

አዎን እግዚአብሄር ዛሬም ይናገራል ግን የሚናገረው በክርስቶስ በኩል ነው ክርስቶስ ደግሞ በቃሉ በኩል ይናገረናል። እነዚህ ቃሉን ተቀብለው ክርስቶስን የታዘዙ ወጌልን ለሌሎች የማስተማር የመስበክ ኃላፊነት አለባቸው። በዚህ መንገድ ጌታ በሰባኪዎች በአስተማሪዎች በወንጌል ፈቃዱን ለሰዎች ይገልጣል በዚህ መልኩ ወደ ጠፉት ይመጣል (ማቴዎስ 11:28~30)

በመጀመሪያ ሥራችን ወንጌልን መስበክ ነው እና በሁለተኛ የሚታዘዙትን በማስተማር መርዳት ነው (ማቴዎስ 28:19~20) ለዚህ ነው ጳውሎስ የሚቀጥለውን የሚነግረን "ለማጥመቅ ክርስቶስ አልላከኝምና ወንጌልን ልሰብክ እንጂ የክርስቶስ መስቀል ከንቱ እንዳይሆን በቃል ጥበብ አይደለም የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሄር ኃይል ነውና" ይላል (1ኛ ቆሮንቶስ 1 :17~18)። እያለ ያለው ለማጥመቅ አልተላኩም የመጀመሪያ ሥራዬ ወንጌልን መስበክ እና የሚታዘዙ ሲገኙ ግን ማጥመቅ መሆኑ ይታወቃል።

ከዚህ በፊት ወንጌልን ሰምተሃል? ካልሰማህ፣ እነሆ የወንጌልን ጥሪ እየሰማህ ነው ወደ ክርስቶስ የሚያመጣህ ጥሪ። ታዘዘው ያድንሃል።

## ጥያቄዎች

1. የተለያዩ የሰዎችን ሀሳብ እግዚአብሄር ሰዎችን ይጠራል ብለው የሚያስቡትን ጥቀስ
2. ጌታ ዛሬ ለሰዎች ይናገራል?
3. እንዴት ነው የሚናገራቸው?
4. ዕብራዊያን 1:1~2 አንብብ
5. እግዚአብሄር በማን በኩል ነው የሚናገረው?
6. ማቴዎስ 17:5 ጥቀስ
7. እግዚአብሄር በቀጥታ ዛሬ ለሰዎች ይናገራል?
8. ዮሐንስ 20:30~31 ምንን ያስተምረናል?
9. እምነት እንዴት ይመጣል?
10. እምነት ከዚህ ውጪ በሌላ መንገድ ይመጣል?
11. ስንት እምነቶች አሉ?
12. ወንጌል በምን ውስጥ ተቀምጧል?
13. የሸክላ ዕቃ የሚለውን አብራራ
14. በሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ጌታ በወንጌል ሰባኪ በኩል ፈቃዱን ለመግለፅ የሠራበትን አንዳንድ ነጥቦች ስጥ
15. ለምንድነው ጌታ ለሰዎች በቀጥታ ለመዳን ማድረግ ያለባቸውን የማይነግራቸው?
16. ማርቆስ 16:15~16 ጥቀስ
17. እኛ እንዴት ነው ወደ ጌታ ዛሬ የተጠራነው?

18. በወንጌል እንዴት ተጠርተናል?
19. እንደ ክርስቲያኖች የኛ ሥራ ምን መሆን አለበት?
20. ጳውሎስ ምን ሊያደርግ ነው የተላከው?

## ትምህርት አራት
## ለወንጌል መታዘዝ

አንድ ሰው ወንጌልን መታዘዝ ይችላል? ወንጌልን መታዘዝ አይቻልም የሚሉ አሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ከዚህ በተቃራኒ ያስተምራል። አስቀድሞ የተስተዋሉ የወንጌል እውነታዎች አሉ እና እኛ ማመን አለብን። እንግዲያውስ የወንጌል ት ዕዛዛት አሉ እነሱም በሚቀጥሉት ትምህርቶች ውስጥ እንመለከታለን እናም እኛም ልንታዘዘው ይገባል።

ይህን ለመጀመር የውንጌልን እውነታዎች ደግመን አፅናኦት እንስጥ። ጳውሎስ በነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ዘርዝሯል “ወንድሞች ሆይ የሰበኩላችሁን ደግሞም የተቀባላችሁትን በእርሱም ድግሞ የቆማችሁበትን በእርሱም ደግሞ የምትድኑበትን ወንጌል አሳስባችሁዋለሁ። በከንቱ ካላመናችሁ በቀር ብታስቡት በምን ቃል እንደሰበኩላችሁ አሳስባቸዋለሁ። እኔ ደግሞ የተቀበልኩትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ እንዲህ ብዬ ፦ መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለኃጥያታችን ሞተ ተቀበረም መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ” (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡1~4)። ይህ እንግዲህ ስለ ክርስቶስ ሞት መቀበርና ትንሳኤ ነው ። ነገር ግን ይህ ከመታዘዝ ጋር ምን አገናኘው? እንደምናየው በጣም ብዙ ነው። አሁን ሐዋሪያው ጳውሎስ በሮሜ ላሉት ክርስቲያኖች ሲፅፍ አድምጡት “ነገር ግን አስቀድማችሁ የኃጥያት ባሪያዎች ከሆናችሁ ለተሰጣችሁለት ለትምህርት ዓይነት ከልባችሁ ስለታዘዛችሁ ከኃጥያትም አርነት ወጥታችሁ ለፅድቅ ስለተገዛችሁ ለእግዚአብሄር ምስጋና ይሁን” (ሮሜ 6፡17~18) እባክህን አስተውል የኃጥያት ባሪያ ወይም አገልጋዮች ነበሩ ከዚያም የፅድቅ አገልጋዮች ሆኑ ለውጡን ምን አመጣው? እንዲያው ይህ ለእነርሱ “ከተሰጠው ትምህርት ከልባቸው ታዘዙ” በሌላ አነጋገር የክርስቶስን ወንጌል ታዘዙ። እዚህ ያለው ትምህርት የሚያመለክተው የክርስቶስን ሞት መቀበር እና ትንሳኤ ነው። ግን በድጋሚ አስተውል የዚያን ትምህርት ዓይነት ታሽዋል። በዚህም ለኃጥያታቸው ሞተዋል ከጌታቸው ጋር በጥምቀት ውሀ ተቀብረው ከውሀው መቃብር ተነስተዋል። ይህ ሁሉ በሮሜ 6 የመጀመሪያ ክፍል ላይ ወጥቶአል እስቲ እናንብብ “ እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ በኃጥያት ጸንተን እንኑርን ? አይደለም። ለኃጥያት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን? ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከርሱ ጋር ተቀበርን። ሞቱንም ብሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትህንሳኤውን በሚመስል

ትንሳኤ ድግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን ከንግዲህስ ወዲያ ለኃጥያት እንዳንገዛ የኃጥያት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንዷተሰቀለ እናውቃለን። የሞጽ ከኃጥያት ፀድቋልና።" (ሮሜ 6፡1~6) ጳውሎስ ቦኃላ በሮሜ 6፡17~18 ላይ እንደገለፀው የታዘዙት የትምህርት ዓይነት ነው። ይህም ብቻ አይደለም ነገር ግን አንድ ሰው ለዚህ ትምህርት ዓይነት በሚታዘዝበት ጊዜ ሁሉ ወይም የጌታን ሞት መቀበር እና ትንሳኤ በድርጊቱ ምሣሌነት ያሳያል።

ስንቀጥል የወንጌል ትዕዛዛት ምን እንደሆኑ እና ከክርስቶስ ሞት መቀበር እና ትንሳኤ ጋር እንዴት እንደሚዛመዱ ማየት እንፈልጋለን። ጌታ እራሱ ሐዋሪያትን "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ያመነ የተጠመቀም ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል" (ማርቆስ 16፡15~16) ማቴዎስ ድግሞ ሲዘግብ "እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃቸሁኋቸው ያዘዝኳቸሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራቸዋቸው ደቀመዛሙርተ አድርጓቸው እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" አላቸው (ማቴዎስ 28፡19~20) ጌታ ወንጌል እንዲሰበክ ትዕዛዝ እየሰጠ መሆኑን ትመለከታላቸሁ። ይህ ብቻ ሳይሆን ግለሰቡ እንዲድን አንዳንድ ትዕዛዛትን ማክበር እንዳለበት ለማሳየት ነው። ከዚያም የጌታን መመሪያ ሲፈጽሙ ሐዋሪያት በኢየሩሳሌም ከተማ ወንጌልን ሲሰብኩ ተገኝተዋል። (ሐዋሪያት ሥራ 2)። በመጀመሪያ ደረጃ ኢየሱስ በእውነት የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎቸንና መረጃዎቸን አቅርበዋል። ህዝቡም ይህን ካመኑ ቦኃላ ነው ይህን ጥያቄ ያቀረቡት "ወንድሞቸ ሆይ ምን እናድርግ?" አሉ (የሐዋሪያት ሥራ 2፡ 37) ከዚያም ጴጥሮስ አንድ ነገር ሊያደርግላቸው መለሰ እንዲ ሲል " ንሰሀ ግቡ ኃጥያታቸሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳቸሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላቸሁ" አላቸው (የሐዋሪያት ሥራ 2፡ 38) ደግሞም ጌታ ለ ሳኦል በተገለጠበት ጊዜ የሐዋሪታ ሥራ 9 ለመዳን ምን ማድረግ እንዳለበት ፈለገ ጌታ ወደ ከተማይቱ እንዲገባ ነገረው እና የሚያደርገው ይነገረሃል አለው። ቦኃላ ሐናኒያ መጥቶ እንዲሁ አደረገ (የሐዋሪያት ሥራ 22፡ 16) በ ሐዋሪያት ሥራ 8 ላይ ፊሊጶስ ለጃንደረባው ክርስቶስን ሲሰብክ አግኝተናል ዘገባውም ጃንደረባው መጠመቅ ፈልጎ እንደጠየቀ ይነግረናል። "ፊሊጶስም ፦ በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዶልሃል አለው። መልሶም ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ሊጅ እንደ ሆነ አምናለሁ አለ። ሰረገላውም ይቆም ዘንድ አዘዘ ፊሊጶስና ጃንደረባው ሁለቱም ወደ ውሀ ወረዱ አጠመቀውም። ከውሀውም ከወጡ ቦኃላ የጌታ መንፈስ ፊሊጶስን ነጠቀው ጃንደረባውም ሁለተኛ አላየውም ደስ ብሎት መንገዱን ይሄድ ነበርና" (የሐዋሪያት ሥራ 8፡37~39) አሁን የውንጌል ትዕዛዛት ምንድናቸው? አንደኛ፣ ወንጌል ሲሰበክ መስማት ሁለተኛ በእግዚአብሄር ማመን አለበት፣ ክርስቶስ ደግሞ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ማመን። ሦስተኛ ከኃጥያቱ ሁሉ ንሰሀ መግባት አለበት፣ አራተኛ እየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ በአፉ መመስከር አለበጥ አምስተኛውም ጥምቀት በጥምቀት በውሀ

ውስጥ በመቀበር መሆን አለበት እርሱም የአጥያት ሥርየት ነው፡፡

በእነዚህ ሀሳቦች በመቀጠል የውንጌልን ትዕዛዛት ሲፈጽም ከዚያም አንድ ሰው ለኃጥያቱ ይሞታል፡፡ ይህም ወንጌልን ሰምቶ ጌታን አምኖአል ከኃጥያቱ ሁሉ ንሰሀ ገብቶአል ወይም ከኃጥያይ ፊቱን አዙሮአል ስለዚህ ይህ ለአጥያት መሞትን ያመለክታል ከዚያም ከሞት ቦኃላ የቀብር ሥነ ሥርዓት አለ እሱም ፊሊጶስና ጃንደረባው ቀብራቸው እንዲፈጸም ወደ ውሀ ሲወርዱ ተመልክተናል፡፡ በተጨማሪም ቆላሲያስ 2፡12 እና ሮሜ 6፡4 ጥምቀት በውሀ ውስጥ መቀበር እንደሆነ ይነግሩናል ከዚያም ከቀብር ቦኃላ ትንሳኤ ይመጣል፡፡ የሐዋሪያት ሥራ 8 ፊሊጶስ እና ጃንደረባው ከውሀ እንደወጡ እናገራል ሮሜ 6 ደግሞ ስለመቃብርና ትንሳኤ ከዚያም መትከልና መነሣት በአዲስ ህይወት ለመመላለስ ይናገራል፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው ለነዚህ ቀላል ትዕዛዛት በመታዘዝ የጌታን ሞት መቀበርና ትንሣኤ የሚያመለክት ግለሰብ አለን፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ክርስቶስን የሚታዘዝ እያንዳንዱ ግለሰብ ሞትን መቀበርን ትንሳኤውን ያሳያል፡፡

በዮሐንስ 3፡3~5 ላይ ክርስቶስ ከውሀ እና ከመንፈስ መወለድን ተናግሮአል፡፡ ይህም ሌላ ተመሳሳይ ነገር ነውና አንድ ሰው በውሀ ሲቀበር በዚያን ጊዜ ከውሀ መውጣት ወይም መወለድ ይሆናልና፡፡ እርሱም ከውሀው መቃብር ትንሳኤ ነው፡፡ እንደዚሁ አንድ ሰው በአዲስ ህይወት ሊመላለስ ይወጣል አሁን በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ሆኖአል (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17)

ትዕዛዛት መከበር አለባቸው እና የጌታን ትዕዛዛት የሚታዘዙ ሰዎች ሽልማት ያገኛሉ ነገር ግን አንድም የወንጌል ትዕዛዛት አላስፈላጊ አይደለም ተብሎ ሊታለፍ እንደማይቻል ያስታውሱ ክዚያ ብቻ ነው እያንዳንዱን ትዕዛዛት ከተከተለ ቦኃላ ጌታ ያንን ያድናል ወደ ቤተክርስቲያኑም ይጨምረዋል ሁሉንም መንፈሳዊ በረከቶችን ይሰጠዋል የዘላለም ህይወት ተስፋም ያገኛል

ምንም እንኳን ወንጌል የሁሉም ቢሆንም እና ድነት እንዲገኝ ሁሉም ተጠያቂ የሆኑ ፍጥረታት ሊታዘዙት የሚገባ ቢሆንም ጳውሎስ ግን በ ምሬት ተናግሯል “ነገር ግን ሁሉ ለምሥራች ቃል አልታዘዙም ኢሳያስ ጌታ ሆይ ምሥክርነታችንን ማን አመን ? ብሎአልና “ ይላል (ሮሜ 10፡16) ይህ በራሱ እንደገና አንድ ሰው ወንጌልን መታዘዝ ብቻ ሳይሆን ለመዳን መታዘዝ አለበት ማለት ነው፡፡ ነገር ግን የማያደርጉትስ ? በዚህ ጉዳይ ላይ እንዲህ ይላል “ ጌታ ኢየሱስ ከሥልጣኑ መላዕክት ጋር ከሠማይ በእሳት ሲገለጥ መከራን ለሚያሳዩአቸሁ መከራን መከራንም ለምትቀበሉ ከእኛ ጋር ዕረፍትን ብድራት አድርጎ እንዲመልስ በእግዚአብሄር ፊት በርግጥ ጽድቅ ነውና እግዚአብሄርን የማያውቁትን ለጌታችንም ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የማይታዘዙትን ይበቀላል በዚያም ቀን በቅዱሳኑ ሊከብር ምሥክርነታችንንም አናችሁዋልና በሚያምኑት ሁሉ ዘንድ ሊገረም ሲመጣ ከጌታ ፊት ከኃይሉም ክብር ርቀው ለዘላለም ጥፋት ይቀጣሉ” (2ኛ ተሰሎንቄ 1 ፡7~9) ስለዚህ እግዚአብሄርን አለማወቅ በሌላ በኩል ደግሞ ወንጌልን አለመታዘዝ ያንኑ ውጤት ማለትም የጌታን በቀል ያመጣል፡፡ ክርስቶስ ለወንጌል የሚታዘዙ ይድናሉ

ያላመኑ ግን ይፈረድባቸዋል ብሏል (ማርቆስ 16፥16) ይህ ሁሉ መዳናቸውን ቸል የሚሉ ማምለጫ የላቸውም ለማለት ነው፡፡ (ዕብራዊያን 2፥2~3)

## ጥያቄዎች

1. አንድ ሰው ወንጌልን መታዘዝ ይችላል?
2. የውንጌልን እውነታዎች ዘርዝር
3. ሮሜ 6፥17~18 አንብብ
4. የሮሜ ሰውች ምንን  ታዘዙ?
5. ትምህርቱ ምን እንዷነበር ግለፅ
6. የክርስቶስን ሞት መቀበርና ትንሳኤ በመታዘዛቸው ውስጥ እንዴት ነው የሣሉት ?
7. ሮሜ 6፥1~6 ምንን ያስትሚራል?
8. ማርቆስ 16፥15~16 እና ማቴዎስ 28፥19~20 ጥቀስ
9. ለምንድነው ጌታ ወንጌል እንዲሰበክ ያዘዘው?
10. መዳን የሚከተል ከሆነ መታዘዝ ያለባቸውን በእነዚህ ጽሁፎች ውስጥ ያሉትን ትዕዛዞች ጥቀስ
11. በሐዋሪያት ሥራ 2 ላይ ሐውሪያቶች የሰበኩትን ተናገር
12. የሐዋሪያት ሥራ 2፥38 አስፈላጊነት ተናገር
13. ፊሊጶስ ለጃንደረባው ምንድነው የሰበከው?
14. የውንጌል ትዕዛዞችን ዘርዝራቸው
15. ለውንጌል ትዕዛዝ መታዘዝ ከጌታ ሞት መቀበር እና ትንሳኤ ጋር እንዴት ይዛመዳል?
16. ዮሐንስ 3፥3~5 እንዴት ከዚህ ጋር ይስማማል?
17. መቼ ነው ጌታ አንድን ሰው የሚያድነው?
18. ማን ነው ወንጌልን መታዘዝ ያለበት?
19. ወንጌልን በማይታዘዙ ላይ ምንድነው የሚከሰተው?
20. እግዚአብሄር ባለማወቅ ይቅር ይላልን?

## ትምህርት አምሥት
## ወንጌልን መስማት

አንድ ሰው የሚሰማው ነገር የሚያምነውን ይወስነዋል፡፡ አንድ ሰው ስህተትን ከሰማ ያንን ስህተት ማመን ይችላል፡፡ በተለይ ቅዱሳት መጽሐፍትን ካልመረመረና እውነትን ለማወቅ ጥረት ካላደረገ የሰማው ስህተት እውነት ሊመስለው ይችላል፡፡ ነገር ግን እውነትን ከሰማ ያንን የሰማውን እውነት የማመን ዕድሉ ከፍተኛ ነው፡፡ ለዚህም ነው ንፁህ የሆነውን የእግዚአብሄርን ቃል መስማት አስፈላጊ የሆነው፡፡ ጳውሎስ እንዲህ ይላል “እምነት ከመስማት ይመጣል መስማትም የእግዚአብሄር ቃል ነው “ (ሮሜ 10፥17) አፅናኦቱ በመስማት ላይ ነው፡፡ ሁሉንም መስማት ሳይሆን

ይልቁንስ የእግዚአብሄርን ቃል መስማት ውጤቱ እምነት ሊሆን ይችላል፡፡
አንድ ሰው እምነቱ በእግዚአብሄር ቃል ላይ የተመሰረተ መሆኑን እንዴት እርግጠኛ ሊሆን እንደሚችል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል፡፡ ብዙ ነገሮች በእግዚአብሄር ስም እንደሚያስተምሩና ብዙ ነገሮች ከመጽሐፍ ቅዱስ ገፆች እንደመጡ ተጠቁመዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ ብዙዎቹ ተቃራኒዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ እነዚህ መለያየት እና ግራ መጋባት ናቸው፡፡ ታዲያ አንድ ሰው የሰማው እውነት መሆን አለመሆኑን እንዴት ማረጋገጥ ይችላል? በጣም ጥሩው መንገድ ወደ ራሱ ውደ ቅዱሳት መጽሐፍት መሄድ ነው፡፡ ማንም ሰው ዬቱንም ያህል ፍቅርና አክብሮት ቢኖረውም የማንንም ስብከት ወይም ትምህርት የመጨረሻ አድርጎ መቀበል የለበትም፡፡ ነፍሳችን በጣም ውድ ናት እናም እምነታችንን እና ድነታችንን በሰው ልጆች ቃል ላይ ለመመስረት ለዘላለማዊነት እርግጠኛ አያደርገንም፡፡ ይልቁንስ ወደ ምንጩ ወድ ራሱ መፅሐፍ ቅዱስ መሄድ አለብን፡፡ ወደ እሱ ከሄድን ቦኃላ በትክክለኛው መንገድ ላይ መሆናችንን ለማረጋገጥ ማንበብ እና ማጥናት ቅዱሳት መፅሐፍትን መመርመር አለብን፡፡ ትክክል ካልሆንን ማረም እንችላለን፡፡
ክርስቶስ እንዲህ አለ “እናንተ በመፅሐፍት የዘላለም ህይወት እንዳላችሁ ይመስላችዋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ እነርሱም ድለእኔ የሚመሰክሩ ናቸው” (ዮሐንስ 5፡39)፡፡ እንደገና ስለ ቤሪያ ሰዎች ቃሉን ከሰሙ ቦኃላ ያደረጕትን እናነባለን “እነዚህም በተሰሎንቄ ከሚኖሩት ይልቅ ልበ ሰፊዎች ነበሩና፥ ነገሩ እንዲዚሁ ይሆንን ? ብለው ዕለት ዕለት መፃሐፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ” (የሐዋሪያት ሥራ 17፡11)፡፡አሁን አስቡ የእግዚአብሄርን ቃል የሚያጠኑ ሰዎች ነበሩ፡፡ ጳውሎስ እውነትን እየሰበከ እንደሆነ ለማየት ከሰበከላቸው ቦኃላ በሱ ዘመን እንኳን ከስብከቱ ቦኃላ ቅዱሳት መፃሐፍትን መመርመር ከቻሉ እኛ ደግሞ ምን ያህል እንዲሁ ማድረግ አለብን፡፡ ዛሬም የዘመናችንን ሰባኪዎች ከሰማ ቦኃላ ሁሉም ይህን ቢያደርግ መፃሐፍትን ቢመረምር ጥሩ አይሆንምን? ይህ ቢሆን ኖሮ ምንም ዓይነት ሃይማኖታዊ ስህተት አይኖርም ነበር በእርግጠኝነት ጥቂት የሐሰት አስተማሪዎች ብቻ ይኖሩ ነበር፡፡
ጳውሎስ ወጣቱን ወንጌላዊ ጢሞቴዎስ የሚባለውን ሲያበረታታ እንዲህ ይለዋል “የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሄር ልታቀርብ ትጋ” (2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡15)፡፡ ለምንድነው ብዙ ሰዎች ለእግዚአብሄር ቃል እውቀት የሌላቸው? ምክንያቱም ቅዱሳት መፃሐፍትን አያጠኑም፡፡ ለምንድነው ብዙ ሰዎች በሃይማኖት ብቻ የሚታለሉት?፣ ምክንያቱም በእውነትና ስህተት መካከል ያለውን ልዩነት ለማወቅ ቅዱሳት መፃሐፍትን አያጠኑም፡፡ ለምንድነው ብዙ ሰዎች በሙሴ ሕግ እና በክርስቶስ ሕግ ግራ የሚጋቡት? ይህም በተመሳሳይ ችግር ነው ቅዱሳት መጽሐፍትን ስለማያጠኑ ሁለቱን ለመለየት ስላልቻሉ ነው፡፡ ወዳጆቼ ! ሐዋሪያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ቃሉን እንዲያጠና ካበረታታው አንተ እና እኔስ እንዲህ ማድረግ የሌለብን ይመስልሃል?

ሐዋሪያው ዮሐንስ በዘመኑ ያሉትን ክርስቲያኖች ሲያበረታታ “ወዳጆች ሆይ መንፈስን ሁሉ አትመኑ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሄር እንደሆኑ መርምሩ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና” ይላል (1ኛ ዮሐንስ 4፡1) እዚህ ጋ ይህ ሐዋሪያ የእግዚአብሄርን ሰዎች አደራ እያለ ያለው መንፈስን ሁሉ አትመኑ ሐሰተኞች ወንገላዊያን እና አስተማሪዎች ወደ ዓለም ወጥተዋልና ይላል። ነገር ግን እዉነተኛውን ከሐሰተኛው ለይተን እንዴት ልናውቅ እንችላለን? እያለ ያለው መርመሩ ነው። እንዴት አድርገን? ስብከታቸውን እና ትምህርታቸውን ከእግዚአብሄር ቃል ጋር በማወዳደር በማመሳከር ነው። ይህንን በታማኝነት ብናደርግ በቀላሉ ማነው እውነተኛ ማነው ሐሰተኛ የሚለውን ማወቅ እንችላለን።

ፊሊጶስ ጃንደርባውን በተገናኘ ጊዜ መጽሐፍ አነበበለት መሆኑን ዘገባው እንዲህ ይላል “ፊሊጶስም አፉን ከፈተ ከዚህም መፅሐፍ ጀምሮ ስለኢየሱስ ወንጌልን ሰበከለት” (የሐዋሪያት ሥራ 8፡35)፣ ውጤቱም ኦሪጂናሉን እምነት እንዲያገኝና ጌታን እንዲታዘዝ አደረገው። በሐዋሪያ ሥራ 8፡5 ላይ ፊሊጶስ ወደ ሰማሪያ ሂዶ ስለክርስቶስ ወንገልን ለህዝቡ እንደሰበከ እናነባለን ቦታላ ላይ ጴጥሮስና ዮሐንስ መጥተው ጎብኝተው ተመሳሳይ ወንጌልን ሰብከው ወደ ኢየሩሳሌም መመለሳቸሀውን እናያለን (የሐዋሪያ ሥራ 8፡25) ስብከታቸው በክርስቶስ እና በእግዚአብሄር ቃል ላይ ብቻ መሆኑን አስተውል።

ወንጌልን የምንሰማው በሁለት መንገድ ነው። በመጀመሪያ ቀድሞ እንደተገለጸው የእግዚአብሄርን ቃል ለራሳችን ስናነብ እና ስናጠና ነው ይህን ስናደርግ ክርስቶስን፣ ጳውሎስን፣ ጴጥሮስንና ሌሎቹንም የእግዚአብሄር ሰውችን የመስማት ዕድሉ እናገኛለን። ነገር ግን በዚህ ዘመን ሁሉም ሰዎች አያነቡም ይህ ማለት እነዚህ ሰዎች በሰባኪያኖች በአፍ የሚነገረውን የእግዚአብሄርን ቃል ብቻ ነው የሚሰሙት በዚህ መንገድ ሁለት ቡድን አለ ስብከትን የሚሰማና ስብከትን የሚሰብክ። ከዚህ የተነሣ ሰባኪ ለመሆን የመረጠው ሰው የእግዚአብሄርን ቃል በጥንቃቄ የመስበክ ትልቅ ኃላፊነት አለበት ። ለመፅሐፉ በጣም ጥንቃቄ ማድረግ አለበት ። የእግዚአብሄርን ቃል በግድለሽነት ወይም በማታለል ወይም በማሳሳት የሚሠሩ ዋጋቸውን ይቀበላሉ። ጳውሎስ የሮሜ ወንድሞቹን መለያየትን የሚፈጥሩትን ለይተው እንዲያውቁና በመልካም ቃልና በሚያማምሩ ንግግሮች የተማሩትን ልቦች እንዳያታልሉ አስጠንቅቋቸዋል (ሮሜ 16፡17~18) ከዚያም ሰሚው የሰማውን ከመቀበሉ በፊት እውነት መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበጥ የእግዚአብሄርን ቃል ማንበብ የሚችሉ ሰዎች ቅዱሳት መጽሐፍትን ለራሳቸው መመርመር ይችላሉ። ማንበብ በማይችሉ ሰዎች ላይ ግን ችግሩ በጣም አሳሳቢ ነው። ታዲያ እነዚህ ምን ሊያደርጉ ይችላሉ? እውነትን እያገኙ መሆናቸውን እርግጠኛ ለመሆን ምንጊዜም ከራሱ ከእግዚአብሄር ቃል በቀጥታ የሚያነብላቸው ሰው ማግኘት አለባቸው። አንድ ሰው በእውነት ማወቅ ከፈለገ እውነትን የመማር መንገድ እንዳለ ጥርጥር የለውም።

ጌታ ሁሉንም ሐዋሪያት ወደ ዓለም ሁሉ ሄደው ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ

እንዲሰብኩ ማዘዙን ማወቅ አስፈላጊ ነው (ማርቆስ 16፡15) እንዷገናም ሄዷው ለአህዛብን ሁሉ እንዲያሰምሩ መዝገቡ ይናገራል (ማቴዎስ 28፡19) ግን ለምን ? የሰው ልጅ ሁሉ ወንጌልን፣ እውነትን፣ የእግዚአብሄርን ቃል ሰምቶ አምኖ እንዲታዘዘው እና እንዲድን ነው፡፡ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲናገር “ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ በእነዚያም ፅና ይህን ብታደርግ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህ “ አለው (1ኛ ጢሞቴዎስ 4፡16) አንድ ሰው በመስማት እንዴት ሊድን ይችላል? ቀደም ሲል እንደተነገረው እምነት የሚመጣው ከመስማት ነው መስማት ደግሞ ወደ እምነት እና መታዘዝ ይመራል፣ እናም መታዘዝ መዳንን ያመጣል፡፡ ጳውሎስ እየተናገረ ያለው ስለዚያ ነው፡፡

በሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም የደህንነት ጉዳዮችን ካነበብክ በእያንዳንዱ ጊዜ የወንጌል ሰባኪ እንደነበረ ትመለከታለሐ ሥራው ምን ነበር ? መዳን ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ወንጌልን መስበክ ነው፡፡ ስለዚህም ወንጌልን በሰሙ ጊዜ አምነው ታዘዙት ከዚያም ድነዋል፡፡ ግን የእግዚአብሄርን ቃል ለመስማት ዕድል ባያገኙስ? ያኔ መዳን ባልቻሉም ነበር ምክንያቱም እምነት የሚመጣው የእግዚአብሄርን ቃል በመስማት ብቻ ነውና ያለ እምነትም እግዚአብሄርን ደስ ማሰኘት አይቻልም (ዕብራውያን 11፡6)

እግዚአብሄር ያኔ ኢየሱስ በተራራ ላይ በተለወጠ ጊዜ ተናግሮአል “በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት” የሚል ድምፅ (ማቴዎስ 17፡5)፣ እንደገና በዛሬው ዘመን እግዚአብሄር እንዴት በልጁ በኩል እንደሚናገር እናነባለን (ዕብራዊያን 1፡1~2)፣ መጨረሻ ላይ ፣ ክርስቶስ ቃል እንደሆነ እናነባለን (ዮሐንስ 1፡ 1~2)፡፡ ስለዚህ የሚያድነን ክርስቶስ እንደሆነ ልንሰማውና ልንታዘዘው የሚገባን ክርስቶስ እንደሆነ ማወቁ አስፈላጊ ነው፡፡ ሰው የተናገረውን እርሳ የሰውን ሀሳብ አስተያየት አስተምሮ ወዘተ እርሳቸው፡፡ ጌታችን ከተነገረው ጋር ሲነፃፀር ከንቱ ናቸው፡፡ ልንሰማው የሚገባን ክርስቶስን ብቻ ነው፡፡ ልንገዛው የሚገባን ክርስቶስን ብቻ ነው፡፡

በመጨረሻ ያዕቆብ የፃፈው “ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁኘምጸሙ ብቻ አትሁኑ” ይላል (ያዕቆብ 1፡22) ንፁህ የሆነውን የእግዚአብሄርን ቃል መስማት አስፈላጊ ቢሆንም፣ እዚህ ማቆም እና መጥፋትም ይቻላል ካልታዘዝነው እውነት በመስማት ብቻ ሊያድነን አይችልም፡፡ ለዚህም ነው ቃሉን ሰሚዎች ብቻ እንዳንሆን የተመከርነው፡፡ ይህንን ብናስታውስ መልካም ነው፡፡

## ጥያቄዎች

1. ብዙውን ጊዜ የሰዎችን እምነት የሚወስነው ምንድነው?
2. እምነት እንዴት ይመጣል?
3. አንድ ሰው እምነቱ በእግዚአብሄር ቃል ላይ መሆኑን እርግጠኛ ሊሆን ይችላል? እንዴት?

4. ሰው መጨረሻ ላይ የሰዎችን አስተምሮ ሊቀበል ይችላል?
5. ዮሐንስ 5፡39 አንብብ
6. የቤርያ ሰዎች ከተሰሎንቄ ሰዎች የበለጠ የታወቁት በምንድነው?
7. የሐይማኖት ስህተት ሊጠፋ የሚችለው እንዴት ነው?
8. ለምንድነው መጽሐፍ ቅዱስ ማጥናት አስፈላጊ የሆነው?
9. የእግዚአብሄርን ቃል ካለማወቅ የተነሳ በሰው ላይ ሊመጣ የሚችለውን የተወሰነ ግለፅ
10. 1ኛ ዮሐንስ 4፡1 ምን ያስተምራል?
11. ፊሊጶስ ለጃንደረባው የሰበከውን ግለፅ
12. ፊሊጶስ ወደ ሰማሪያ የሄደው ለምንድነው?
13. በዬትኞቹ ሁለት መንገድ ነው ወንጌል የሚሰሙት?
14. ጌታ በሰባኪው ላይ ስለሚሰብከው ነገር ኃላፊነት ይጥልበታል?
15. ማንን ነው ልንሰማ የሚገባን?
16. ክርስቶስ ዛሬ የሚናገረው እንዴት ነው?
17. ምን ዓይነት ሰሚዎች መሆን አለብን?
18. መቼ ነው እውነት የሚያድነው?

## ትምህርት ስድስት
## በእግዚአብሄር ማመን

የእብራዊያን ፀሐፊ እንዲህ ይላል "እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው።" (ዕብራዊያን 11፡1)። እምነት ደግሞ መተማመን መታመን መቀበል እና መታዘዝ የሚያመጣ ነው ሊባል ይችላል። በዚህ መሠረት ላይ ነው አንድ ሰው ክርስቲያን የሚሆነው እና አንድ ክርስቲያን ሆኖ የሚቀረው በእምነት ምክንያት ነው።

እንደገና ይሄው የእብራዊያን ጸሐፊ "ያለ እምነትም እግዚአብሄርን ደስ ማሰኘት አይቻልም። ወደ እግዚአብሄር የሚደርስ እግዚአብሄር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋል" (ዕብራዊያን 11፡6) እባክህን በእግዚአብሄር ማመን ውስጥ ሁለት ነገሮች እንዳሉ ልብ በል። አንደኛ፦አንድ ሰው እግዚአብሄር እንዳለ ማመን አለበት ሁለተኛ እግዚአብሄር እሱን ለሚሹት እንደሚሸልመው ማመን አለበት ። እንግዲህ አንድ ሰው ከነዚህ እምነቶች አንዱን ቢጎድል እንዴት ተቀባይነት ይኖረዋል?

በዙሪያችን ስንመለከት እና ያሉትን ነገሮች ሁሉ ስናይ በሰማይ ውስጥ አምላክ እንዳለ ማመን እንዴት መረዳት እንችላለን? ሰማይ፣ ምድር፣ እንስሳት፣ የሰው ህይወት እና እነዚህ ነገሮች ሁሉ ፈጣሪን ያመለክታሉ። ዳዊት ሲናገር "ሰማያት የእግዚአብሄርን ክብር ይናገራሉ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል" (መዝሙር 19፡1) "ሰነፍ በልቡ አምላክ የለም ይላል። በሥራቸው ረከሱ ጎሰቆሉ በጎ

ነገርን የሚሠራ የለም” ይላል (መዝሙር 14፡1)
እግዚአብሄር እንዳለ ማመን ብቻ በቂ አይደለም። ዳሩ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መኖኑንም ማመን አለብን ክርስቶስ ራሱ እንዲህ ብሏል “ልባቸሁ አይታወክ በእግዚአብሄር እመኑ በእኔም ደግሞ እመኑ” (ዮሐንስ 14፡1) ብዙ ዓይነት ጥቅሶቸ የሚመሳሰሉ አሉ አሁን ይህን ኣዳምጥ “በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሄር አንዲያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲው ወዷልና” (ዮሐንስ 3፡16) “ኢየሱስም ጮሆ ፦ በእኔ የሚያምን በላከኝ ማመኑ ነው እንጂ በእኔ አይደለም” አለ (ዮሐንስ 12፡44)።

በክርስቶስ የማያምኑስ ? ቅዱሳት መፅሐፍትም ስለነዚህ ሰዎቸ ይነግሩናል። ክርስቶስ ሲናገር “ በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፣ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሄር ሊጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል” (ዮሐንስ 3፡18)፣ “በልጁ የምያምን የዘላለም ህይወት አለው፣ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሄር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ህይወትን አያይም” (ዮሐንስ 3፡36)፣ “እንግዲህ በኃጥያታቸሁ ትሞታላቸሁ አልኋቸሁ፣ እኔ እንደሆንኩ ባታምኑ በኃጥያታቸሁ ትሞታላቸሁና አላቸው” (ዮሐንስ 8፡24)።

ከላይ ከተጠቀሱት የቅዱሳት መፃሐፍት ጥቅሶቸ፣ በጌታ በማመን የሚገኘውን በረከት በእርግጥ እናያለን፣ ነገር ግን እርግማኑ ወዮታው እና በርሱ ላለማመን በመረጡት ላይ የሚደርስባቸውን ማየት እንቸላለን።

ግን እስከምን ድረስ በእግዚአብሄር እና በክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ ብለን እናምናለን? በአዕምሮ ልንቀበላቸው እንቸላለን፣ ግን ይህ በቂ ነው? የእግዚአብሄር ቃል እምነታቸንን ማሳየት ወይም ማረጋገጥ እንዳለብን ይነግረናል። ለምሣሌ ክርስቶስ ሲናገር “ስለምን ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ ትሉኛላቸሁ፣ የምለውንም አታደርጉም” አላቸው (ሉቃስ 6፡46)እንደገናም እንዲህ ይላል “በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም፣ በዚያ ቀን ብዙዎቸ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን ? በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግምን? ይሉኛል የዚያን ጊዜም ከቶ አላወቅኋቸሁም እናንተ ዓመፀኞቸ፣ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ” ይላል (ማቴዎስ 7፡21~23) አሁን እነዚህ ሰዎቸ አማኞቸ ነበሩ፣ እና ከዚህም በተጨማሪ በሐይማኖታዊ ልምምዶቸ ላይ ተሰማርተው ነበር ነገር ግን ምንድነው ስህተቱ? ስህተቱማ በመንግስተ ሰማያት ያለውን የአባትን ፈቃድ እየሠሩ ስላልሆነ ነው።

በጌታ ማመን ያለብን እርሱ የሚናገረውን እስከምናደርግ ድረስ ነው። እምነት ብቻ አያድንም እምነት ብቻውን የሞተ ነውና። ያዕቆብ ይህን ሲናገር እንዲህ ይላል “እንዲሁም ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው” ይላል (ያዕቆብ 2፡17)፣ ቀጥሎ ድግሞ “ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲፀድቅ ታያላቸሁ” ይላል (ያዕቆብ 2፡24)፣ በመጨረሻ “ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው” ይለናል (ያዕቆብ 2፡26)፣ አሁን ይህ በመንፈስ

ቅዱስ አነሳሽነት የፃፈው ፀሐፊ በእነዚህ የተለያዩ ፅሁፎች ውስጥ ሥራም ከእምነት የበለጠ አስፈላጊ እንደሆነ አሳይቶናል።ይህንን ዘገባው ይደግፈዋል። አንዳንድ ጊዜ የእምነት ሰባኪዎች እና አስተማሪዎች ዮሐንስ 3፡16 እንደ የአቋም ምሣሌ ብቻ አድርገው ይጠቅሳሉ። ሆኖም ክርስቶስ ስለእምነት ብቻ በዚህ ጥቅስ ውስጥ የተናገረው ነገር የለም። ይልቁንም በእግዚአብሄር ካመን እንደማንጠፋ ነገር ግን ዘላለማዊ ህይወት እንደምንቀበል አሳየን። ግን ጥያቄው አንድ ሰው እውነታውን አውቆ በእግዚአብሄርና በቃሉ ካመነ ምን ያደርጋል? የሚለው ነው በርግጥ ጌታን ይታዘዛል ይህ ነው ዋናው ነጥቡ።

አዎን መፅደቅ በእምነት ነው (ሮሜ 5፡1) ነገር ግን በእምነት ብቻ አይደለም። በፀጋው የዳንነው በእምነት ነው (ኤፌሶን 2፡8~9) ነገር ግን በእምነት ብቻ አይደለም።በርግጥ አንድ ሰው በእምነት ብቻ ይድናል ብሎ አይከራከርም፣ ከንስሐ፣ ከጥምቀት፣ ከክርስቲያናዊ ህይወት ወዘተ ካልሆነ በስተቀር እምነትን ብቻ ለመስበክ አንገደድም። በርግጥ ችግሩ በሙሉ በእምነት ትርጉም ላይ ነው፣ እና መፅሐፍ ቅዱስ የሚናገረው የእምነት ዓይነት ንቁ እምነት፣ ተንቀሳቃሽ እምነት፣ የሚሠራ እምነት፣ እና ታዛዥ እምነት ነው።ኢየሱስ በሽተኛን ወደ እርሱ ያመጡትን ሰዎች እምነት በተመለከተበት ቦታ ላይ እናነባለን (ማቴዎስ 9፡2) ይህን በተግባር እንድናሳይ ወይም እንድናረጋግጥ የሚፈልገው በድርጊታችንና በትዕዛዛቱ በመታዘዝ ነው። ያለበለዚያ እምነታችን ከንቱ እና የሞተ ነው።

እምነት ከክርስቶስ ወንጌል ትዕዛዛት ውስጥ አንዱ ነው። የእግዚአብሄርን ቃል በመስማት ይመጣል (ሮሜ 10፡17) ግለሰቡ ከኃጥያቱ ንሰሐ እንዲገባ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ እንዲመሰክር እና ለኃጥያት ሥርየት እንዲጠመቅ ይመራዋል፣ እና እነዚህንም እያንዳንዳቸውን በሚከተለው ትምህርት እናሰውላለን። ነገር ግን ያለዚህ እምነት አይቻልም ለዚህ እምነት ሲታዘዙ በእውነተኛ እምነት መታዘዝ ወዲያውኑ ይመጣል። የጌታ ትዕዛዛት አያጠራጥርም። ነገር ግን ይከበራል ትንህርቱን አይቃወምም፣ ነገር ግን ይታዘዛል።

ክርስቶስ እንዲ አለ "ያመነ የተጠመቀም ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል" (ማርቆስ 16፡16)፣ አንድ ሰው ጌታን አልታዘዝም ብሎ አለማመን እንደሚችል የታወቀ ነው። በተመሳሳይ ጊዜ ካመነ ክርስቶስን ይታዘዛል ያም ማለት ይጠመቃል ማለት ነው። ያ በጣም ቀላል ነው፣ አይደለም እንዴ? እንጊድያውስ የሐዋሪያት ሥራ መፅሐፍ ውስጥ በመለወጥ ጉዳይ ውስጥ ሁሉ ለኃጥያተኛው የሚሰብክ ሰባኪ አለ። የሰባኪውን ስብከት ሰምቷል። እንጌልን አምኖአል፣ በኃጥያቱ ተፀፅቶአል፣ ክርስቶስን መስክሮአል ከዚያም ተጠመቀ። ከዚያስ ምን ተፈጠረ? ግለሰቡ አንዴ ወንጌልን ሰምቶ ወደ ማመን ከደረሰ በቀረው ላይ ምንም ችግር የለበትም ምክንያቱም አሁን የጌታን ትዕዛዝ ለመታዘዝ ዝግጁ ነውና። ሁሉም ነገር ማለትም ሐሳቡ የሚያያዘው በማመኑ እና አለማመኑ ላይ ነው።

በሐዋሪያት ሥራ 2 ላይ ስለማያምኑት ቡድን እናነባለን። ከነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹ በስቅለቱ ውስጥ ትክክለኛ ተሳትፎ ነበራቸው። ከዚያም ጴጥሮስና

ሌሎቸ ሐዋሪያት ወንጌልን ሰበኩላቸው። ክርስቶስ በእውነት የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን አሳይተዋል። ከዚያም ስለዚህ ጉዳይ ካሳመናቸው በኃላ ጥያቄው ቀላል ነበር።

"ምን እናድርግ" ነበር ያሉት (ሐዋሪያት ሥራ 2፡37)፣ በሌላ አነጋገር፣ አሁን በእምነታቸው ላይ ለመሥራት ተዘጋጅተው ነበር፣ እና ሦስት ሺ የሚያህሉት አደረጉት (ሐዋሪያት ሥራ 2፡41) ሌላ ዘገባ ፊልጶስ ለሳማሪያዊያን ወንጌልን እንደሰበከ ይናገራል ብዙዎቸም አምነው ተጠመቁ (የሐዋሪያት ሥራ 8፡12) ፊሊጶስ ክርስቶስን ለጃንደረባ በሰበከ ጊዜ ዘገባው እንደሚናገር አምኖ ምን እንደሚያደርግ ሲነገረው ሰምቶ ታዞ ደስ እያለው መንገዱን ቀጠለ። (የሐዋሪያ ሥራ 8፡26~39) ፣ በሐዋሪያት ሥራ 16 ላይ ጳውሎስና ሲላስ ለእስር ቤቱ ጠባቂ ወንጌልን ሲነግሩት ለመዳን ምን ማድረግ እንዳለበት መጠየቁን የሚነግረን አለን። እርሱ ግን ያላመነ ሰው ነበረ፣ ስለዚህ ያምኑ ዘንድ ለእርሱና ለቤተሰቦቹ የእግዚአብሄርን ቃል ሰበኩላቸው በዚህም ምክንያት የወይኒው ቤት ጠባቂ ቁስላቸውን አጥቦ ንሰሐም ገብተው ወዲያው እሱና ቤተሰቡ እንደተጠመቁ ታሪኩ ይነግረናል።

በመጨረሻም ቅዱሳት መፃሐፍት የሚያስተምሩት አንድ እምነት ብቻ ነው።(ኤፌሶን 4፡5) ፣ አንድ መፃሐፍ ቅዱስ ብቻ አለ እና ሁሉም ሲቀበሉት እና ሲያምኑት ያን ጊዜ ሁላችንም አንድ እምነት ይኖረናል፣ እናም አንድ እምነት ሁላችንንም ወደ አንድ ነገር ይመራናል ያም ጌታን መታዘዝ እና ለርሱ ታማኝ መሆንን።

**ጥያቄዎቸ**

1. እምነት ምንድነው?
2. እምነት አስፈላጊ ነው ? ምን ያህል?
3. ዕብራዊያን 11፡6 ግለፅ
4. በእግዚአብሄር ማመን ለምስ አስፈለገ?
5. አንድ እግዚአብሄር መኖሩን ማመን ብቻውን በቂ ነው?
6. በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን እንዳለብን የሚገልፅ የተወሰኑ ጥቅሶቸን ስጥ
7. በክርስቶስ በማያምኑት ላይ ምን ይፈጠራል?
8. እስከምን ድረስ ነው አንድ ሰው በክርስቶስ ማመን ያለበት?
9. በአዕምሮ ብቻ ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን ማመን በቂ ነው? ካልሆነ ለምን?
10. ለክርስቶስ መታዘዝን የሚገልፅ የተወሰነ ግለፅ
11. ሁሉም የሐይማኖት ቡድኖቸ ድነዋል?
12. እምነት ብቻ ማለት ምንድነው?
13. ያዕቆብ 2 አንብብና በሰፊው ተወያዩበት

14. ዮሐንስ 3፡16 እምነት ብቻ ያስተምራል?
15. በትክክል በክርስቶስ የሚያምን እያንዳንዱ ምን ማድረግ አለበት?
16. በእምነት ፀድቀሃል?
17. መጽሐፍ ቅዱስ ምን ዓይነት እምነት ያስተምራል?
18. እምነትን በምን ማረጋገጥ እንችላለን ?
19. እምነት እንዴት እንደሚመጣ ተናገር
20. እምነት ወደ ዬት ያመራል?
21. የክርስቶስ ትዕዛዝ አጠያያቂ ነው?
22. ማርቆስ 16፡16 አንብብና ግለፀው
23. በሁሉም የመለወጥ ጉዳዮች ላይ ምን ተመልክተዋል?
24. ሰዎች ካመኑ በኃላ ምን ማድረግ አለባቸው?
25. ስንት ዓይነት እምነት አለ?
26. እምነታችን ወደ ዬት ይመራናል?

## ትምህርት ሰባት
## ለኃጥያት ንሰሀ

ሌላው የወንጌል ትዕዛዝ ንሠሀ ነው፡፡ ነገር ግን ንሠሀ ምንድነው እና ለክርስቶስ ሞት መቀበር እና ትንሳኤ ጋር ምን ትርጉም አለው? በመጀመሪያ ንሠሀ የሚለው ቃል እንደገና መመለስ፣ ወደ ሌላ አቅጣጫ መሄድ፣ መለወጥ፣ መጥፎና ስህተት የሆነውን ነገር ማድረግን ማቆም ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ በአንድ ወቅት አሁን እየተናገርን ያለነውን የሚገልፅ ታሪክ ተናግሯል “ነገር ግን ምን ይመስላችዋል? አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት ወደ አንደኛው ቀርቦ ልጄ ሆይ ዛሬ ሂድና በወይኔ አትክልት ሥራ አለው፣ እርሱም መልሶ አልወድም አለ ቦኃላ ግን ተፀፀተና ሄደ፣ ወደ ሁለተኛውም ቀርቦ እንዲሁ አለው፣ እርሱም መልሶ እሺ ጌታየ አለው ነገር ግን አልሄደም፣ ከሁለቱ የአባቱን ፈቃድ ያደረገ ዬትኛው ነው? ፊተኛው አሉት፣ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፦ እውነት እአችዋለሁ ቀራጮችና ጋለሞቶች ወደ እግዚአብሄር መንግሥት በመግባት ይቀድሟችዋል ዮሐንስ በፅድቅ መንገድ መጥቶላችሁ ነበርና አላመናችሁበትም ቀራጮችና ጋለሞቶች ግን አመኑበት እናንተም ይህን አይታችሁ ታምኑበት ዘንድ ቦኃላ ንሠሀ አልገባችሁም” አላቸው (ማቴዎስ 21፡28~32)፣ ከክርስቶስ ሞት መቀበር እና ትንሳኤ ጋር ስላለው ግንኙነት አንድ ሰው ከኃጥያቱ ሲመለስ የጌታ ሞት ምሣሌ ነው፡፡ ስለዚህም በሁለቱም ሁኔታዎች ንሠሀ ለምን በጣም አስፈላጊ እንደሆነ እናያለን፡፡

ሰው ኃጥያተኛ መሆኑን አውቆ (ሮሜ 3፡23)፣ የኃጥያትም ደመወዝ ሞት እንደሆነ (ሮሜ 6፡23) በማወቅ ክርስቶስ እንግዲህ አንድ ሰው ንሰሀ መግባት ወይም መጥፋት እንዳለበት ተናግሯል (ሉቃስ 13፡3)፣ ይህንኑ አፅናኦት ለመስጠት በሉቃስ 13 ፡5 ላይ ያንኑ ቃል ደጋግሞ ተናግሮአል፡፡ በሌላ አነጋገር አንድ ሰው ንሰሀ ካልገባ በቀር እንደሚጠፋ ሊድን እንደማይችል ነው፡፡ዳግመኛም እንዲህ አለ ፦

“እላችዋለሁ እንዲሁ ንሰሀ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ፃድቃን ይልቅ ንሰሀ በሚገባ በአንድ ኃጥያተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል” አለ (ሉቃስ 15፡7)

ይሁን እንጂ ንሰሀ መግባት ለአንድ ሰው ኃጥያት ከማዘን በላይ እንደሆነ ተረዳ። አንድ ግለሰብ ተይዞ እስር ቤት በመግባቱ ሊያዝን ይችላል የሚያዝነው ግን ለጥፋቱ ስለከፈለው ዋጋ ነው። ይህ ንሰሀ አይባልም ስለሠሩት ነገር መፀፀት ነው ይህም ምድራዊ ፀፀት ይባላል። ጳውሎስ ሲነግረን “እንደግዚአብሄር ፈቃድ የሆነ ሀዘን ፀፀት የሌለበትን ወደ መዳንም የሚያደርሰውን ንሰሀ ያደርጋልና የዓለም ሀዘን ግን ሞትን ያመጣል” (2ኛ ቆሮንቶስ 7፡10) አምላካዊ ሀዘን ወይም ፀፀት ወደ ንሰሀ ሊመራ ይችላል።

ማነው ንሰሀ የሚገባው? ጳውሎስ በአቴና ሲያልፍ በስብከቱ ማገባደጃ እንዲህ ነበር ያለው “እንግዲህ እግዚአብሄር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንሰሀ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል ቀን ቀጥሮአልና፣” (የሐዋሪያት ሥራ 17፡30)፣ ስለዚህ በዚህ መሰረት ጌታ በሁሉም ቦታ ያሉ ሰዎች ሁሉ ንሰሀ እንዲገቡ ወይም ከኃጥያታቸው እንዲመለሱ ይፈልጋል፣ እንዲሁም እግዚአብሄር በአንድ ወቅት አንዳንድ ነገሮችን በአለማወቅ የሰሩትን ችላ ብሎ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ባለማወቅም ሆነ በማወቅ የተደረገም ቢሆን እግዚአብሄር ማብኛውንም ኃጥያት እንደማይታገስ ወይም ችላ እንደማይል ግልፅ አድርጓል። ዳግመኛ ሐዋሪያው ጴጥሮስ ሲናገር “ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደ ሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፣ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንሰሀ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፉ ወዶ ስለእናንተ ይታገሳል። (2ኛ ጴጥሮስ 3፡9)

ወደ ንሰሀ ስለሚመጡት ሁሉ ሲናገሩ፣ ቅዱሳት መፅሐፍት እነዚህ ግለሰቦች ሰዎች ወይም ኃጥያት የሠሩ መሆናቸውን ይገልፃሉ። ይህ ሕፃናትን ወይም ልጆችን እንኳን አይጨምርም ምክንያቱም እንዲህ ያሉ ለመንግሥተ ሰማያት ናቸው።(ማቴዎስ 18፡1~3) ይልቁንም ወንጌሉ የተላለፈው ከኅጥያታቸው ንሰሀ ለመግባት የደረሱ ሰዎች ሲሆን ይህም ማለት መጥፎ ድርጊታቸውን ያውቁና ከእነሱ መመለስ ይፈልጋሉ ማለት ነው። ይህንን ማድረግ የሚችሉት የተጠያቂነት ዕድሜ ላይ የደረሱ ብቻ ናቸው።

አሁን ወደ ሐዋሪያት ሥራ 2 ስንሄድ ጴጥሮስና ሐዋሪያ በበዓለ ሃምሣ ቀን ለሰዎች ሲሰብኩ አንብበናል። እነሱም ለኃጥያተኞች እሰብኩ ነበር፣ በክርስቶስ ስቅለት እንኳ ተካፋይ ለነበሩት ሰብከዋል እንግዲህ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለማወቅ በፈለጉ ጊዜ ጴጥሮስ “ጴጥሮስም፦ ንሰሀ ግቡ ኃጥያታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፣ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ” (የሐዋሪያት ሥራ 2፡38)፣ በሌላ ጊዜ አገልግሎትም “እንግዲህ ከጌታ ፊት የመፅናናት ዘመን እንድትመጣላችሁ አስቀድሞም ለእናንተ የመረጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲልክላችሁ ኃጥያታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንሰሀ ግቡ” (የሐዋሪያት ሥራ 3፡19)

ከነዙህ የቅዱሳት መፅሐፍት ጥቅሶች በመነሳት ንሰሐ ከወንጌል ትዕዛዛት

አንዱ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ ያም ማለት አንድ እና ሁሉም ጌታን ለመታዘዝ እና የኃጥያታቸው ሥርየት እንዲያገኙ ከጠበቁ ከኃጥያታቸው መመለስ አለባቸው ወይም በሌላ መንገድ አንድ ፃድቅ ሊድን እና ያለ ንሰሀ ወደ ሰማይ ሊሄድ አይችልም፡፡ ጥሩ የሞራል ህይወት ብቻውን በቂ አይደለም መዳንን ለማግኘት አንድ ሰው ማድረግ ያለበትን ጌታ የተናገረውን ለማድረግ የሚተካ ምንም ነገር የለም፡፡ በሐዋሪያት ሥራ መፅሐፍ ውስጥ ገብተህ ሌሎቸን የንሰሀ ጉዳዮችን ካጠናህ እና ከግምት ውስጥ ስታስገባ የምታነባቸውን ለምሣሌ በሐዋሪያት ሥራ 16 ላይ ጳውሎስና ሲላስ የጌታን ቃል ለእስር ቤቱ ጠባቂ እና ለቤተሰቡ ከሰበኩ ቦኃላ ወስዶ ቁስላቸውን እንዳጠበ ይናገራል፡፡ ያ ንሰሐ ካልሆነ ምን ሊሆን ይችላል? በሳኦል ጉዳይ በሐዋሪያት ሥራ 9 መሠረት ክርስቲያኖቸን አሳዳጅ ነበር፣ ነገር ግን አንድ ጊዜ ጌታ ከተገለጠለት ቦኃላ የተለየ ሰው ሆነ፣ ለወንጌል መታዘዝ ብቻ ሳይሆን ከዚያም ሲጀመር አጥብቆ የተቃወመውን ክርስቶስንና ስቅለቱን መስበክ ጀመረ ይህ ንሰሐ አይደለምን?

አንድ ሰው ወንጌልን በመታዘዝ የልብ ለውጥ አለ፣ ይህም በእምነት፣ የህይወት ለውጥ ንሰሀን የሚያካትት እና የመንግሥቱ ለውጥ ይህም የጥምቀት ውጤት እንደሆነ ተናግሯል፡፡ በንሰሀ እና ለክርስቶስ በመታዘዝ እንግዲህ የአንድ ሰው ኃጥያት ይሰረይለታል ወይም ይታጠባል፡፡ አዲስ ፍጥረት ሆኗል (2 ቆሮንቶስ 5፡ 17) በክርስቶስ አዲስ ሰው ሆነ (ገላትያ 3:26~27) ቀድሞ ያደረጋቸውን ነገሮቸ ከንግዲህ ወዲህ አያደርግም፡፡ በዚህ ዓለም ውስጥ እንደዚህ ያለ ምንም ነገር የለም፡፡

አንድ ጊዜ ክርስቲያን ከሆነ ቦኃላ እንደገና ንሰሐ የሚገባበት ጊዜ ሊኖር ይችላል፡፡ ክርስቲያን ፊፁም አይደለም ታማኝ ክርስቲያን እንኳን ሊሳሳት ይችላል፡፡ ሆነ ብለው ኃጥያት የሚሠሩ ሰዎቸ ስህተታቸውን በመናዘዝና ይቅር እንዲላቸው ወደ አምላክ መፀለይ አለባቸው (ያዕቆብ 5፡16፣ ሐዋሪያት ሥራ 8፡22) ካልሆነ ግን ይጠፋሉ፡፡

ነገር ግን ክርስቲያን ያልሆኑ ገና የ ቤተክርስቲያን አባል ያልሆኑ ክርስቶስን ሰምተው በእርሱ ማመን፣ ከሓጥያታቸው ንሰሐ ገብተው ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ መስክረው ለኃጥያታቸው ሥርየት መጠመቅ ይስፈልጋቸዋል፡፡ እነዚህ እያንዳንዳቸው ትዕዛዛት አስፈላጊ ናቸው፡፡ በአንዱ ብቻ ማን ሊድን አይችልም ወይም ከእነሱ ያለሌሎቹ አንዱን በመተው መዳን አይቻልም ንሰሐን በተመለከተ አንድ ሰው እያንዳንዱን ኃጥያት እና ሁሉንም ስህተቶቸ ሌላው ቀርቶ ሐይማኖታዊ ስህተቶቸን መተው አለበት ማለት ነው፡፡ ህይወቱ ባታዛዥነት እንዲቀጥል ለማስቻል አንድ ሰው የንሰሐን ትዕዛዝ እንደታዘዘ ሊናገር የሚቸለው ከዚያ ቦኃላ ብቻ ነው፡፡

## ጥያቄዎቸ

1. ንሰሐ ምን እንደሆነ ግለፅ

2. ንሰሐ ከክርስቶስ ሞት መቀበር እና ትንሳኤ ጋር ምን ዝምድና አለው?
3. ሰው በምን እና እንዴት ይመደባል?
4. ሉቃስ 13፡3 ጥቀስ
5. አንድ ሰው ንሰሐ ካልገባ ምን ይሆናል?
6. አንድ ሰው ንሰሐ ሲገባ የሚደሰተው ማን ነው?
7. ንሰሐ ማለት ስለ ሠሩት ስህተት አዝናለሁ በማለት ብቻ ይገለፃል?
8. አምላካዊ ፀፀት ወይም ንሰሐ ምን እንደሆነ ግለፅ
9. ንሠሐ መግባት ያለበት ማን ነው?
10. 2ኛ ጴጥሮስ 3፡9 አንብብና አስረዳ
11. ንሰሐ ህፃናቶቸን ይመለከታል?
12. ወንጌል ቀጥታ የሚመለከተው ማንን ነው?
13. ሐዋሪያ ሥራ 2፡38 እና ሐዋሪያ ሥራ 3፡19 አንብብና ንሠሐ ምን እንደሆነ ተወያዩበት
14. ንሠሐ በወንጌል እንደአንድ ትዕዛዝ ሆኖ ተመዝግቧል?
15. አንድ ሰው መልካም ባህሪይ ስለአለው ወደ መንግስተ ሰማይ ሊደርስ ይቸላል?
16. በሐዋሪያ ሥራ 16 እና ሐዋሪያ ሥራ 9፣ ላይ ንሠሐ እንዴት እንደተገለፀ አሳይ
17. ንሰሐ እንዴት አድርጎ የህይወት ለውጥን ያመጣል?
18. አንድ ሰው ክርስቲያን ከሆነ ቦኋላ ሌላ ጊዜ ንሠሐ ያስፈልገዋል?
19. አንድ ሰው ንሠሐ ሳይገባ የክርስቶስን ወንጌል መታዘዝ ይቸላል?

## ትምህርት ስምንት
## ክርስቶስን መመስከር

ሌላው በወንጌል ውስጥ ከታዘዙት ውስጥ ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን መመስከር ነው። መመስከር የሚለው ቃል ማሳወቅ፣ ማወጅ፣እውቅና መስጠት፣ እምነትን በመግለፅ ማለት ነው።ይህ ደግሞ ከማንኛውም ወንጌልን ከሚታዘዝ ሰው ጌታ የሚጠብቀው ጉዳይ ነው። ማንም ሰው ይህንን ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን የሚገልፀውን የመፅሐፍ ቅዱስ ዘገባ ለማመን ፈቃደኛ መሆን አለበት ። እነዚህን አምኖ ለመመስከር ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም በእንደዚህ ዓይነት መልኩ ካልተቀበለ ይህ ሰው ወንጌልን ለመታዘዝ ዝግጁ አይደለም ማለት ነው፣

ክርስቶስ የዚህን አስፈላጊነት ሲያስተምር እንዲህ አለ “ስለዚህ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፣ በስው ፊትም የሚክደኘን እኔ ደግሞ በሰማያት ላይ ባለው አባቴ ፊት እክደዋለሁ” አለ (ማቴዎስ 10፡32~33) ስለነዚህ ጥቂት እንመልከት

1. ሁሉም ክርስቶስን እንዲመሰክር ተጋብዘዋል። ማንም ይሁኑ ከዬትም

ይሁኑ ለውጥ አያመጣም፣ ሁሉም ተጋብዘዋል። ይህ እውነት አሁንም የፀና ነው።

2. ምስክርነቱ ክርስቶስን እንጂ የሰው ኃጥያትን አይደለም፣ ጌታ መጀመሪያ የሰውየውን ታማኝነት ይፈልጋል ከዚያም ጌታ ነው ከሰውየው ኃጥያት ጋር የሚገናኘው

3. ይህ ጌታን መመስከር በሰው ፊት መሆን አለበጥ ለዚህ የሚሰሙ ምስክሮች ሊኖሩ ይገባል፣ አንድ ሰው በእውነት በክርስቶስ የሚያምን ከሆነ በእርሱ ያለውን እምነት ሁሉም እንዲያውቁ ይፈልጋል

4. ጌታ በሰማያት ባለው አብ ፊት ሊመሰክርለት ቃል የገባለት ያ ሰው ክርስቶስን በሰው ፊት ሊመሰክር የፈቀደ ግለሰብ ነው። የእግዚአብሄር ልጅ በሰማያት ባለው አባቱ ፊት እንዲመሰክርለት የታደለን ሰው በረከቱን ክብሩን አስብ። ስለዚህ ጌታ ከሰዎች ምንን ይጠይቃል? በሰው ፊት እንዲመሰክር ብቻ ነው።

5. በሰዎች ፊት የማይመሰክሩ ወይም የሚክዱት በሰማይ አባቱ ፊት ይክዳቸዋል፣ ነገር ግን እሱን አለመመስከራቸው ብቻ አይደለም አይደለም ነገር ግን ክደዋል፣ እና እሱም ይክዳቸዋል ይህ ማንንም ቢሆን ማለት ነው።

ስለዚህ በእነዚህ ሁለት አጭር የቅዱሳት መፃሕፍት ጥቅሶች ውስጥ ብዙ ተብሏል። ጌታ ሁለቱንም ወገኖች፣ በረከቶችን እና ውጤቶቹን እሱን ለሚክዱ ሰዎች አሳይቷል። በተመሳሳይ ጊዜ እያንዳንዱ ሰው ለራሱ እንዲወስን ለራሳቸው ለስዎች ይተዋል።

እነዚህ ክርስቶስን ስለማይመሰክሩ ሰዎችስ? ሐዋሪያው ዮሐንስ እንዲህ ይላል “ብዙ አሳቾች ወደ ዓለም ገብተዋልና እነርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ የማያምኑ ናቸው፣ ይህ አሳቹና የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው” ይለናል (2ኛ ዮሐንስ 7)፣ “መላስም ሁሉ ለእግዚአብሄር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመስክር ዘንድ ነው” (ፊሊጵስዩስ 2፡11)

በመቀጠል፣ ይህ ምስክርነት በአፍ ብቻ ሳይሆን ለመዳን የተደረገ መሆኑን እናስተውላለን “ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሄርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህ፣ ሰው በልቡ አምኖ ይፀድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና” (ሮሜ 10፡9~10)፣ አሁን አንዳንዶች ለመዳን አንድ ሰው ማድረግ ያለበት ኃጥያቱን መናዘዝ እና ጌታን መቀበል ብቻ ነው እናም ይህ መጨረዛ ነው ብለው ይናገራሉ ይህ ግን ስህተት ነው። ግን እምነትስ ? ነገር ግን አንድ ሰው ምስክርነቱ በእምነት ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ያስባል ታዲያ ስለንሰሐስ? እዚህ ቦታ ስለንሰሐ የተባለ የለም፣ ስለዚህ ቀላሉን መንገድ ለማግኘት የሚፈልጉ ሁሉ ነገሮችን በዚህ መልኩ ይመለከታሉ። ነገር ግን በጣም ቀጣዩ ጥቅስ እምነት እና ክርስቶስን መመስከር ከድነት እቅድ ጋር እንዴት እንደሚስማማ ያሳያል። በመጀመሪያ አንድ ሰው በልቡ እንዴት ማመን እንዳለበት ነገር ግን ለፅድቅ ወይም ለመዳን መሆኑን ያሳያል። ያም ማለት አንድ ሰው አልዳነም ነገር ግን ወደ መዳን እየተመለከተ ነው ወይም መዳንን እየጠበቀ ነው። በሁለተኛ በአፍ

መመስከር ለመዳን መሆኑን ያስረዳል። እዚህ ያለው ምስክርነት ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ እና እንደገና ለመዳን እንጂ ድኖ አይደለም፣ እናም ወደ መዳን የሚሄደው እና የዳነ ትልቅ ልዩነት አለው። በሌላ አነጋገር፣ በክርስቶስ ማመን፣ እና ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ መመስከር መዳንን ለማምጣት በቂ አይደሉም። አንድ ሰው ያለእምነት እና ያለ ምስክርነት ሊድን አይችልም ነገር ግን ሌሎች የሚሠራቸው አሉ።

በመጨረሻም አንድ ሰው ለጥምቀት ተስማሚ የሆነ ርዕሰ ጉዳይ ለማድረግ ይህን ምስክርነት እንዲሰጥ የተፈለገበትን አንድ ምሣሌ አለን፣ወደ ራሱ ወደ መፅሐፉ እንሂድ "የጌታም መልዓክ ፊሊጶስን፦ ተነስተህ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው ምድረ በዳ ወደ ሆነ መንገድ ሂድ አለው፣ ተነሥቶም ሄደ፣ እነሆም ህንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ በገንዘቧ ሁሉ ላይ የሰለጠነ አንድ የኢትዮጵያ ሰው ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር ሲመለስም በሰረገላ ተቀምጦ የንቢዩን የኢሳያስን መፅሐፍ ያነብ ነበር መንፈስም ፊልጶስን ፦ ወደዚህ ሰረገላ ቅረብና ተገናኝ አለው። ፊሊጶስም ሮጦ የነቢዩን የኢሳያስን መፅሐፍ ሲያነብ ሰማና ፦"በእውኑ የምታነበውን ታስተውላለህን?" አለው። እርሱም "የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል? አለው። ወጥቶም ከእርሱ ጋር ይቀመጥ ዘንድ ፊሊጶስን ለመነው። ያነበውም የነበረ የመፅሐፉ ክፍል ይህ ነበር  እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ፣ የበግ ጠቦትም በሸላቹ ፊት ዝም እንደሚል እንድሁ አፉን አልከፈተም። በውርደቱ ፍርዱ ተወገደ፣ ህይወቱ ክምድር ተወግዳለችና ትውልዱንስ ማን ይናገራል?  ጃንደረባውም ፊሊጶስን መልሶ ፦እባክህ ነቢዩ ይህን ስለማን ይናገራል? ስለራሱ ነውን? ወይስ ስለሌላ አለው። ፊሊጶስም አፉን ከፈተ ከዚህም መጽሐፍ ጀምሮ ስለኢየሱስ ወንጌልን ሰበከለት ። በመንገድም ሲሄዱ ወደ ውሀ ደረሱ፣ ጃንደረባውም ፦ እነሆ ውሀ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድነው? አለው። ፊሊጶስም በፍፁም ልብህ ብታምን ተፈቅዶልሃል አለው። መልሶም ፦ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ አለ። ሰረገላውም ይቆም ዘንድ አዘዘ ፊሊጶስና ጃንደረባው ሁለቱም ወደ ወረዱ አጠመቀውም፣ ከውሀውም ከወጡ ቦኃላ የጌታ መንፈስ ፊሊጶስን ነጠቀው ጃንደረባውም ሁለተኛ አላየውም ደስ ብሎት መንገዱን ይሄድ ነበርና " (የሐዋሪያት ሥራ 8፡26~39)፣ አሁን እዚህ ምን እንደተፈጠረ ግልፅ ይመስላል፣ ፊሊጶስ ይህንን ሰው ስለክርስቶስ እና እርሱን ለመታዘዝ ምን ማድረግ እንዳለበት አስተማረው እርሱም ከተማረ ቦኃላ ፈቃዱን ለመፈፀም ፈለገ ነገር ግን አስተውል እርሱን ከማጥመቁ በፊት ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ አምኖአል፣ ይህ ግን ብቻውን አላዳነውም መጨረዛ ተጠመቀ።

ከዚህ ምሣሌ በመነሣት ክርስቶስን መመስከር የሚመለከቱትን ሌሎች የቅዱሳት መጻሐፍት ጥቅሶችን በማክበር ማንንም ከማጥመቃችን በፊት ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ ያምናል ወይ ብለን እንጠይቀዋለን ከዚያም መልሱ አዎን ከሆነ ወደ ጥምቀቱ መግባት እንችላለን።

ይህ ምስክርነት ብዙውን ጊዜ እንደመልካም ምስክርነት ተብሎ ይጠራል እናም በእውነቱ ማንኛውም ምስክርነት ጥሩ ምስክርነት ተብሎ ሊጠራ ከቻለ ይህ ዋነኛው ይሆናል።

ታዲያ ምን እንላለን? አንድ ሰው ለመዳን ወንጌልን መስማት፣ ማመን፣ ከኃጥያቱ ንሠሀ መግባት፣ ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ መመስከር እና በመጨረሻም ለኃጥያት ሥርየት መጠመቅ አለበት ። በዚህ ጉዳይ ላይ የክርስቶስ ምስክርነት ከሁሉም በላይ የሆነው የደህንነት እቅድ አካል ወይም ከወንጌል ትዕዛዛት አንዱ ብቻ ነው። እርሱም ብቻ ማንንም አያድንም፣ አስፈላጊ እና ኃይለኛ የሚሆነው ባስቀመጠው ቦታ ላይ ሲቀመጥ ብቻ ነው። ትዕዛዛቱን ሁሉ ጠብቆም ነው

## ጥያቄዎች

1. መመስከር የሚለውን ቃል ምን ማለት እንደሆነ ግለፅ
2. የእግዚአብሄር ልጅ ለመሆን እንዲቾል አንድ ሰው ምን መመስከር አለበት?
3. ማቴዎስ 10፡32~33 አንብብና ተወያዩበት
4. ክርስቶስን ለመመስከር የሚጋበዙት እነማን ናቸው?
5. የት ነው ምስክርነቱ የሚከናወነው?
6. ክርስቶስ ደግሞ እንደውጤት እሱን ሲመሰክሩት ምን ያደርጋል?
7. እሱን መመስከር የካዱት ምን ይሆናሉ?
8. ምስክርነት እንዴት ይደረጋል?
9. ምስክርነት ለመዳን ነው ወይስ በመዳን ነው? ልዩነቱ ምንድነው?
10. ፊሊጶስ ጃንደረባውን ከማጥመቁ በፊት ምን ነበር የፈለገው?
11. መቼ ነው የመሰከረው? ምን ነበር የመሰከረው?
12. ይህ ምስክርነት ለምን አስፈለገ?
13. ዛሬ መጠመቅ ለሚፈልግ ሰው ተመሳሳይ ምስክርነት እንዲያደርግ የመጠበቅ መብት አለን?
14. ብዙውን ጊዜ ይህ መመስከር ምን ይባላል?
15. የደህንነትን ዕቅድ አብራራ ግለፅ

## ትምህርት ዘጠኝ
## ለኃጥያት ሥርየት መጠመቅ

በዘመናት ካሉት በጣም አወዛጋቢ ጉዳዮቾ አንዱ የጥምቀት ጉዳይ ነው። ነገር ግን የመፅሐፍ ቅዱስ ርዕስ ጉዳይ ነውና ከወንጌል ትዕዛዛት አንዱ ነው። ከሌሎቹ ትዕዛዛት የበለጠ አስፈላጊ አይደለም ግን በተመሳሳይ ጊዜ እንደ ሌሎቹ ሁሉ አስፈላጊ ነው። እያንዳንዱ የሚፈልገውን ደህንነት የሚያመጣውን ለትዕዛዞቾ በሙሉ በመታዘዝ ነው።

በዚህ ትምህርት ስለጥምቀት የምንችለውን ያህል እንማማራለን፣ ትርጉሙን ለማወቅ በመሞከር እንጀምራለን ይህ ይልቁንስ ቀላል ነው፡፡ ጥምቀት የሚለው ቃል የመጣው ባፕቲዞ ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም መጥለቅ መስጠም መቀበር ውስጥ መጥለቅ ተብለው ይታወቃሉ፡፡ መፅሐፍ ቅዱሳችንም ይህን ይደግፋል “ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን ? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ህይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን” (ሮሜ 6፡3~4)፣ “በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ በጥምቀት ድግሞ ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሄር አሠራር በማመናችሁ ከርሱ ጋር ተነሳችሁ” (ቆላሲያስ 2፡12) ግን ስለመርጨት እና ስለማፍሰስ ምን ተባለ? ይሄ የሰዎች ድርጊት ወይም ሀሳብ ተብሎ የሚወገድ ነው፡፡ እነሱ የመጥለቅ ልምድን ለመተካት አስተዋውቀዋል፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሄርን ቃል የሚያከብሩ ሰዎች በፊፁም ሊቀበሉት አይችሉም፡፡

በመቀጠል በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለልዩ ልዩ ጥምቀቶች እናነባለን፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ጳውሎስ በኤፌሶን 4፡5 ላይ ጥምቀት አንዲት ብቻ እንደሆነች ፅፏል፡፡ እሺ አሁን ዛሬ አስገዳጅ ወይም ግዴታ የሆነ ጥምቀት የትኛው ነው? እስቲ ወደ ሐዋሪያ ሥራ 8፡26~39 ስንመለስ የፊሊጶስንና የጃንደረባውን ታሪክ እናነባለን፡፡ ፊሊጶስ ይህንን ሰው ስለክርስቶስ እና ፍቃዱ ካስተማረው ቦኃላ ከዚያም መጠመቅ ፈለገ ይላል ዘገባው “በመንገድም ሲሄዱ ወደ ውሐ ደረሱ፣ ጃንደረባውም፦ እነሆ ውሀ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድነው? አለው፣ ፊሊጶስም በፍፁም ልብህ ብታምን ተፈቅዶልሃል አለው፣ መልሶም አየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ሊጅ እንደ ሆነ አምናለሁ አለ፡፡ ሰረገላውም እንዲቆም አዘዘ ፊሊጶስና ጃንደረባው ሁለቱም ወደ ውኃ ወረዱ አጠመቀውም፣ ከውኃውም ከወጡ ቦኃላ የጌታ መንፈስ ፊሊጶስን ነጠቀው፣ ጃንደረባውም ሁለተኛ አላየውም ደስ ብሎት መንገዱን ይሄድ ነበርና” (የሐዋሪያት ሥራ 8፡36~39) አሁን ጥቂት እንመልከታቸው፦

1. ጥምቀት የመጣው ለዚህ ሰው ለጌታ ታዛዥነት የመጨረሻ ደረጃ ነው፡፡
2. ይህ በመቀበር ነበር እና በውኃ ውስጥ መቀበሩን ከውኃው በመውጣታቸው አወቅን፡፡
3. ነገር ግን በዚህ ነጥብ ላይ ለመጨቃጨቅ ቦታ አይኖርም ነበር ምክንያቱም ዘገባው ሲናገር ሁለቱም ወደ ውኃ ውስጥ እንደወረዱ ይናገራልና፡፡ የበለጠ ግልፅ ለማድረግ ፊሊጶስንና ጃንደረባውን ይመለከታል ከዚያም ነጥቡን ወደ ቤት ለመንዳት ሁለቱም ከጥምቀቱ ቦኃላ ከውኃ ውስጥ ወጡ ይላል፡፡ አሁን ይህንን ማን ይከራከራል? የጌታን ቃል እንዳለ የማይቀበል ካልሆነ በቀር፡፡

ከዚያም ወደ ዮሐንስ 3፡3~5 ስንመለስ ቅዱሳት መፃሐፍት የሚሉን አለ “ኢየሱስም መልሶ፦ እውነት እውነት እልሃለሁ፣ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሄርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው፣ ኒቆድሞስም፦ ሰው ከሸመገለ

በኃላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማዕፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን? አለው፣ ኢየሱስም መለሰ፦ነንዲህ ሲል እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃ እና  ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሄር መንግሥት ሊገባ አይችልም" (ዮሐንስ 3፡3~5)፣ አሁን ውኃ በአንድ ሰው መዳን የሚጫወተው ሚና ቀላል ነው። ስለጥምቀት እና በትክክል ከግምት ውስጥ የሚገባውን ነገር ይመለከታል። መንፈስ በእግዚአብሄር ቃል ሲመራው በጥምቀት ዳግመኛ ይወለዳል (1ኛ ጴጥሮስ 1፡23)፣ ይህ እንደ 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13፣ ሮሜ 6፡3~4 እና ሌሎችም ይህ ድርጊት አንድን ሰው ወደ ጌታ መንግሥት ወይም ቤተክርስቲያን ወይም ወደ ክርስቶስ እንደሚመራ ከሚነግሩን ቅዱሳት መጻሐፍት ጋር እንደሚገጣጠም እናውቃለን

እንደገናም ጳውሎስ ለቲቶ ሲጽፍ "እንደ ምህረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ  እኛ ስላደረግነው በፅድቅ ስለነበረው ሥራ አይደለም" (ቲቶ 3፡5) እዚህ ጋ በአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብ የሚለው የውኃ ጥምቀትን ያመለክታል፣ በትክክል የሚያወራውም ይህ ነው።ስለዚህ ጥምቀት በመቀበር ነው መቀበርም በውኃ ውስጥ ነው ይህም በቅዱሳት መጻሐፍት የምናነበውና ዛሬም እያደረግን ያለነው ነው።

የጥምቀትን አስፈላጊነት በተለያዩ ብዙ ጥቅሶች ስናነብ የምናገኛቸው ነው፣ ለምሣሌ፣ እንደሚያድን "ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት  ምሣሌው ሆኖ አሁን ያድነናል፣ የሰውነትን እድፍ ማስወገድ አይደለም ለእግዚአብሄር የበጎ ህሊና ልመና ነው እንጂ" (1ኛ ጴጥሮስ 3፡21)፣ ሃዋሪያው ጥምቀት ብቻውን ያድናል እያለ አይደለም ነገር ግን ጌታ ካስተማራቸው ትዕዛዞች ጋር ሆኖ እንደሚያድን ነው። እንደገና ክርስቶስ እራሱ "ያመነ የተጠመቀም ይድናል፣ ያላመነ ግን ይፈረድበታል" (ማርቆስ 16፡16)ብሏል። መቼ ነው ጥምቀት የሚያድነው? አንድ ሰው አምኖ ሲጠመቅ። ይህንን መካድ ማለ ክርስቶስን መካድ ማለት ነው።

በመቀጠልም ጥምቀት ለኃጥያት ስርየት እንደሆነ  እናነባለን "ንሠሀ ግቡ ኃጥያታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ  በኢየሱስ ክርስቶስ  ስም ተጠመቁ ፣ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ" (የሐዋሪያት ሥራ 2፡38) ሳኦልም እንዲጠመቅና ኃጥያቱ በዚህ ጥምቀት እንዲታጠብ ተነግሮታል "አሁን ለምን ትዘገያለህ  ተነሣና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ ከኃጥያትህም ታጠብ" (የሐዋሪያ ሥራ 22፡16)፣ እንደገናም የጌታ ትዕዛዝ ነው "በክርስቶስ ኢየሱስ ስም እንዲጠመቁ አዘዛቸው" (የሐዋሪያ ሥራ 10፡48)

ከመዳን ከኃጥያት ስርየት ወዘተ በተጨማሪ አንድ ጊዜ ከክርስቶስ ደም ጋር የተገናኘው  በዚህ መታዘዝ ነው፣ ይህም አንድ ሰው የኃጥያት ይቅርታ እንዲያገኝ ያስችለዋል ለዚህም የማቴዎስ ወንጌል 26፡28 አለን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም የፈሰሰው ለኃጥያት ሥርየት ነው። ነገር ግን ጴጥሮስ በበዓለ ሃምሳ ቀን ለሰዎች የኃጥያታቸውን ስርየት  ማግኘት ከፈለጉ ንሠሀ ገብተው መጠመቅ እንዳለባቸው ሲነግራቸው እነዚህን ቀላል ትዕዛዛት  በመጠበቅ አንድ ሰው ከደሙ ጋር ይገናኛል

ማለት ነው፣ የኃጥያቱ ስርየት ከክርስቶስ ደም ጋር ነው፡፡ እንደገና በኤፌሶን 1፡7 እና በቆላስያስ 1፡4 ላይ አንድ ሰው የኃጥያት ሥርየት የሚያገኘው በክርስቶስ ደም እንደሆነ ተናግሯል፣ ሳኦል ግን ኃጥያቱ እንዲታጠብ ወይም እንዲሰረይ ተነግሮታል በዚህ በጥምቀት መታጠብ ማለት ነው ስለዚህ በጥምቀት ሥራ ኃጥያትን ከሚያፀዳው ክክርስቶስ ደም ጋር  እንደሚመጣ አንድ ጊዜ ግልፅ ነው፣ እርግጥ ነው ወደ ሮሜ ሰዎች ምዕራፍ 6 ከክርስቶስ ሞት ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን ተነግሮናል፣  ይህ ማለት በመታዘዝ ከጌታ ሞት ጥቅሞች ጋር እንገናኛለን ማለት ነው፡፡

በመቀጠል፣ በጥምቀት ወደ ክርስቶስ እንደምንገባ ተነግሮናል ጳውሎስ ለገላቲያ ወንድሞች ሲፅፍ  "በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጆች ናችሁና፣ ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችዋል" (ገላቲያ 3፡26~27)

ዳግመኛም ጥምቀት ብቻ ማዳን እንደማይችል ነገር ግን አንድም ሰው ሳይጠመቅ ሊድን እንደማይችል  አፅናኦት ይሰጣል፡፡ በቅዱሳት መጻሐፍት ውስጥ አንድ ግለሰብ እንደ ዳነና ቦኃላ እንደተጠመቀ  ምንም ትምህርት የለም አንድ ሰው ጥምቀት ምን እንደሆነ ብቻ ሳይሆን የጥምቀትን ዓላም መረዳት አለበት አንድ ሰው ደርዘን ሙሉ በጥልቀት ቢጠመቅ ነገር ግን ለትክክለኛ ዓላማ ካልተጠመቀ ዋጋ የለውም ለዚህ ነው የጥምቀትን ዓላም ማወቅ አለበት የምንለው፡፡ አንዲት ጥምቀት ብቻ አለች እሷም የመፅሐፍ ቅዱስ  ለኃጥያት ሥርየት የሆነችሁ በመቀበር የምንጠመቀው እና ያንን ስናደርግ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወደ ምናነበው ቤተክርስቲያን የምታስገባ ናት፣ ያ ካልሆነ ማሾፍ ብቻ ይሆናል፡፡

ነገር ግን ጥምቀት መቼ ነው የሚያድነው?  እያንዳንዱ ንፁህ የክርስቶስን ወንጌልን ሲሰማ፣ ሲያምን በትክክለኛው ከኃጥያቱ ንሠሀ ሲገባ፣ ክርስቶስን የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን ሲመሰክር ከዚያ ቅዱሳን መጻሐፍት እነደሚያዙት ሲጠመቅ ነው የሚድነው፣ ከዚህ ጊዜ ቦኃላ ብቻ ነው ጥምቀት ሊያድን የሚችለው፡፡ በሌላ አነጋገር ይህ የመጨረሻ የመታዘዝ ትዕዛዝ  ሲተረጎም ክክርስቶስ ውጪ ወደ ክርስቶስ ውስጥ የምንገባበት ነው፡፡ የመጨረሻ ደረጃ ነው፣ ወሳኝ ደረጃ ሆኖ አንድን የዳነ ሰው ወደ ክርስቶስና ወደ ቤተክርስቲያኑ የሚጨመርበት ድርጊት ነው፡፡

በመጨረሻ በጥምቀት ሥራ አንድ ሰው የክርስቶስን መቀበር ለመምሰል በውኃ ውስጥ ተቀብሮ ትንሳኤውን ለመምሰል ከውኃ መቃብር ውስጥ በመውጣት በአዲስ ህይወት የሚመላለስበት ነው ጥምቀጥ ይህ የክርስቶስ መቀበርና ከመቃብር መነሣት ምስል ወይም ምሣሌ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ የጌታን መንገድ የምንመረምርበት ሌላ ክንዋኔ የለም፡፡ ሮሜ 6 በሚገባ አንብብ፡፡

**ጥያቄዎች**

1. በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት በጣም አወዛጋቢ ጉዳዮች አንዱ

ምንድነው? ለምን ?

2. ጥምቀት በወንጌል ውስጥ የታዘዘ ነው?
3. ጥምቀት ከሌሎቹ ትዕዛዞች የበለጠ በጣም አስፈላጊ ነው?
4. ሰው ሁሉ እንዲድን የሚል ትዕዛዝ አለ?
5. ጥምቀት የሚለውን ቃል ግለፅ
6. ሮሜ 6፡3~4 እና ቆላስያስ 2፡12 ምንን ያስተምራሉ ?
7. መርጨት እና ማፍሰስ የሚባለው ምንድነው?
8. ስንት ዓይነት ጥምቀቶች አሉ?
9. አንዱ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥምቀት ምንድነው?
10. የሐዋሪያት ሥራ 8፡26~39 አንብቡና ተወያዩበት
11. ጃንደረባው በምን ውስጥ ተቀበረ?
12. ዮሐንስ 3፡3~5 መቀበርን እንዴት አድርጎ ያስተምራል?
13. በአዲስ ልደት መታጠብ ማለት ምን ማለት ነው?
14. ጥምቀት ምን ማለት እንደሆነ ግለፅ
15. ጥምቀት ያድናል? ጥምቀት ብቻውን ያድናል?
16. ማርቆስ 16፡16 ጥቀስ
17. አንድ ሰው የኃጥያት ስርየትን ለማግኘት ምን ማድረግ አለበት?
18. ጥምቀት ታዟል?
19. አንድ ሰው ከክርስቶስ ደም ጋር እንዴት ይገናኛል?
20. ማቴዎስ 26፡28 እና የሐዋሪያት ሥራ 2፡38 ተውያዩበት
21. እንደዚሁም ኤፌሶን 1፡7 እና የሐዋሪያት ሥራ 22፡16 ተወያዩበት
22. በክርስቶስ ሞት መጠመቅ ማለት ምን ማለት ነው?
23. አንድ ሰው በምን መንገድ ነው ወደ ክርስቶስ የሚገባው?
24. አንድ ሰው በተሳሳተ ዓላማ ውኃ ውስጥ መቀበር ይችላል?፣ ካልሆነ ምን ማድረግ አለበት?
25. ጥምቀት መቼ ነው የሚያድነው?
26. እንዴት ነው የክርስቶስ መቀበር እና ትንሳኤ ከጥምቀት ጋር የሚመሳሰለው?

## ትምህርት አሥር
## የወንጌል በረከቶች

የወንጌል እውነታዎች እና ከወንጌል ትዕዛዛት በተጨማሪ የወንጌል በረከቶች አሉ፡፡ እርግጥ ነው እውነታውን ማመን ትዕዛዛቱም መከበር አለባቸው፡፡ እናም በረከቱን የሚቀበሉት ወንጌልን የሚያምኑ እና የሚታዘዙ ብቻ ናቸው፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስ እንዲህ ይላል “በክርስቶስ በሰማያዊ ሥፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ” (ኤፌሶን 1፡3)፣ እንደዚሁም ለሮሜ ወንድሞች ሲፅፍ “ወደ እናንተም ስመጣ በክርስቶስ በረከት

ሙላት እንድመጣ አውቃለሁ” ይላል (ሮሜ 15፡29)

እነዚህ በረከቶች ምንድናቸው? ብዙ እና በርካታ ናቸው፣ ነገር ግን የተወሰኑትን ለማየት እንሞክራለን።

1. በክርስቶስ ኢየሱስ ወንጌል በማመን አንድ ሰው የኃጥያቶቹን ስርየት ይቀበላል “ጴጥሮስም፦ ንሰሐ ግቡ ኃጥያታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ” (የሐዋሪያት ሥራ 2፡38)፣ ይህም ሌላው የመዳን መንገድ ነው ።(ማርክ 16፡16)፣ እናም ዳግም ይወለዳል (ዮሐንስ 3፡3~5)፣ ይህ እንዴት አስደናቂ ነው አንድ ሰው ኃጥያቱ ታጥቦለት አዲስ ሰው ሆኖ አዲስ ህይወትን መኖር መጀመሩ።

2. በወንጌል በኩል አንድ ሰው ወደ ክርስቶስ ይገባል፣ “ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? “ (ሮሜ 6፡3)፣ “በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጆች ናችሁና፣ ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችዋል” (ገላቲያ 3፡26~27)፣ “ስለዚህም ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፣ አሮጌው ነገር አልፎአል፣ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል” (2ቆሮንቶስ 5፡17)፣ ምክንያቱም እኛ በክርስቶስ የሆንን ሁሉንም መንፈሳዊ በረከቶችን የጌታ የሆኑትን ሁሉ ተቀብለናል።

3. ወንጌልን በመታዘዝ ወደ አካሉ ወይም ወደ ቤተክርስቲያኑ ተጨምረናል፣ በ1ኛ ቆሮንቶስ 12 ላይ ሐዋሪያው ጳውሎስ የክርስቶስ አካል እንደሆንን ሲነግረን በርግጥም አካል ማለት ቤተክርስቲያን ናጥ (ቆላስያስ 1፡18፣ ኤፌሶን 1፡22~23)፣ ይህንን ሲገልፅ ወንጌል ታዘን ስንጠመቅ ወደዚህ አካል እንደምንጨመር ይገልፃል። “አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን ባሪያዎችም ብንሆን ጨዋዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና፣ ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል” (1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13)፣ ቤተክርስቲያን በዓለም ላይ ትልቁ ተቋም ነው፣ አይፈርስም ግን ለዘላለም ፀንቶ ይቆማል፣ የዚህ አካል ክፍል መሆን የዚህ ቤተክርስቲያን በመሆን መባረክ እንዴት አስደናቂ ነው።

4. እኛ አሁን የእግዚአብሄር ልጆች ነን፣ ክርስቲያኖቸም ነን “ክርስቲያን እንደሚሆን ግን መከራን ቢቀበል ስለዚህ ስም እግዚአብሄርን ያመስግን እንጂ አይፈር” (1ኛ ጴጥሮስ 4፡16) ለምን ? ምክንያቱም በክርስቶስ ስም ውስጥ ደህንነት አለ፣ “መዳንም በሌላ በማንም የለም፣ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ከሰማይ በታች ሌላ የለምና” (የሐዋሪያ ሥራ 4፡12) ስለዚህ ቆም ብለህ አስብ በክርስቶስ በማመናችን ትምህርቱን በመታዘዛችን እሱን እስክንለብስ ድረስ አከበረን፣ ይህ ራሱ በራሱ ትልቅ በረከት ነው።

5. እንደ ክርስቲያን ጌታን ለማምለክ ደግሞ መብቱና ሥልጣኑ አለን፣ “ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኖአል፣ አብ ሊሰግዱለት እንደነዚህ ያሉትን ይሻልና፣ እግዚአብሄር

መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል" (ዮሐንስ 4፡23~24) ይህን እንድናደርግ እንድንሰባሰብና እንድናመልከው አስጠንቅቆናል "በአንዳንዶቹም ዘንድ ልማድ እንደሆነው መሰብሰባችንን አንተው እርስበርሳችን እንመካከር እንጂ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ" (ዕብራዊያን 10፡25)፣ በእያንዳንዱ የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ጌታን ለማምለክ ከጌታ ህዝብ ጋር መገናኘት መቻል እንዴት ያለ ዕድል እና ክብር ነው፡፡ ይህንን እንደ እንጂ እንደ መፍትሔ እንጂ እንደ ተግባር ልንቆጥረው አይገባም፡፡ ጌታ እራሱ የተከበረ እንግዳቸን እንደሚሆን ቃል ገብቷል እና በእርግጠኝነት እሱ አብሮን ነው፣ እራሱ እንዲህ ብሏልና "እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፊፃሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" (ማቴዎስ 28፡20)

6. ከዚያም የህብረት በረከት አለ "በሐዋሪያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየፀሎቱም ይተጉ ነበር" (የሓዋሪያት ሥራ 2፡42) እኛ ክርስቲያኖቸ የእምነት ባለንጀሮቻችን ሊሰጡን የሚችሉትን እርዳታና ማበረታቻ እንፈልጋለን፡፡ ይህ የሣምንታዊው ጉባኤ ዓላም አንዱ ነው፣ እንዲህ ባለው ማህበር፣ አምልኮ እና ሥራ ሊመጣ የሚቻለው ኅብረት በራሱ ትልቅ በረከት ሊሆን ይቻላል፡፡

7. እኛ ክርስቲያኖቸ ሌላው የመፀለይ መብት በማግኘት የተባረክን ነን፡፡ እግዚአብሄር የሰው ልጅን ሁሉ ፀሎት አይሰማም፣ቅዱሳት መፅሐፍት ሲነግሩን "እግዚአብሄርን የሚፈራ ፈቃዱንም የሚያደርግ ቢኖር ያንን እግዚአብሄር ይሰመዋል እንጂ ኃጥያተኞችን እንዳይሰማ እናውቃለን" (ዮሐንስ 9፡31)፣ በሌላ አነጋገር ፀሎት የተሰጠው ለእግዚአብሄር ልጆች  እግዚአብሄርን እንደ አባታቸው የቀረቡትን ፣ ይሁን እንጂ ፀሎቱ እንዲሰማና ልመናው እንዲፈፀምለት ፀሎቱ ከእግዚአብሄር ፈቃድ ጋር የሚስማማ መሆን አለበት ፡፡ "በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፣ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን የሰማናል" (1ኛ ዮሐንስ 5፡ 14)፣ እንደዚሁም የዕብራዊያን ፀሐፊ ሲፅፍ "እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ፀጋ እንድናገኝ ወደ ፀጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ" (ዕብራዊያን 4፡16)፣ እዚህ እየተናገረ ያለው ስለፀሎት ታላቅ በረከት ነው፣ ፍላጎቱ፣ ችግር ወይም ምንም ይሁን ምን ወደ ጌታ መፀለይ የሚያስፈልገን ምንም ይሁን ምን ምን ያህል አመስጋኞች መሆን እንዳለብን አውቀን ወደ እርሱ ልንወስደው እንችላለን፡፡ ልጆቹን ነንና ስናናግረው እሱ ርኅሩኅ እና አስተዋይ እንደሆነና ልመናችንን በዚህ መሰረት እንደሚፈፅምልን እናውቃለን፡፡

8. በሣምንቱ የመጀመሪያ ቀን ጌታን ለማስታወስ የጌታ እራትን በመውሰድ በረከት አለን፣ ጳውሎስ ሲናገር "የምንባርከው የበረከት ፅዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት አለው አይደለምን? የምንቆርሰውስ እንጀራ ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? (1ኛ ቆሮንቶስ 10፡16)፣ ስለእኛ ለሞተልን ሥጋውንና ደሙን እያሰብን ለእርሱ ክብር መስጠት መቻላችን በእውነት ትልቅ መንፈሳዊ በረከት ነው፡፡

9. ለክርስቶስ ወንጌል በመታዘዝ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ተቀብለናል፡፡

እንደገና የሐዋሪያት ሥራ 2፡38 በመጥቀስ ጴጥሮስ በንሰሐና በጥምቀት የኃጥያታችን ስርየትና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንደምንቀበል ተናግሯል፡፡ እግዚአብሄር ክርስቶስ እና መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ መኖር አቻ የሌለው በረከት ከዚህ የበለጠ ምን ክብር ሊሰጠን ይችላል?

10. ለጌታ መኖር፣ በምድር ላይ እሱን መወከል የመቻል በረከት አለ "እግዚአብሄር አብን በእርሱ እያመሰገናችሁ፣ በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት" (ቆላሲያስ 3፡17)፣ ክርስቶስ እራሱ "ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሄርን መንግሥት ፅድቁንም ፈልጉ፣ ይህም ሁሉ ይጨመርላችዋል" አለ (ማቴዎስ 6፡33)

11. እኛም ጌታ ሁልጊዜ ከእኛ ጋር እንደሚሆን እናውቃለን፡፡ እውነትን ከማስተማር እና ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለመቀየር እኛ ለሌሎች እና ለመላው ዓለም ወንጌልን እንሰብካለን፣ ለመላው ዓለም ለደህንነት ዓላም ከመሆን የበለጠ ምን በረከት ሊኖር ይችላል? ይህም ብቻ ሳይሆን የጌታን ፈቃድ ለማደስ በምንጥርበት ጊዜ እርሱ አሁንም ሁልጊዜም ከእኛ ጋር እንደሚሆን ቃል እንደገባልን ማወቅ ምንኛ የምያፅናና ነው፣ አሁን እርሱን ስሙት "እንግዲህ ዩዱና አህዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችዋቸው ያዘዝኳችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችዋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው፣ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" (ማቴዎስ 28፡19~20)

12. በመጨረሻም ጌታ ትዕዛዛቱን ከጠበቅን እና ለእርሱ ታማኝ ከሆንን የህይወት አክሊል ወይም የዘላለም ህይወት እንደሚሰጠን ቃል ገብቷል "ወደ ህይወት ዛፍ ለመድረስ ሥልጣን እንዲኖራቸው በደጆቹዋም ወደ ከተማይቱም እንዲገቡ ልባቸውን የሚያጥቡ ብፁአን ናቸው"( ዮሐንስ ራዕይ 22፡14) "እስክሞት ድረስ የታመንህ ሁን የህይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ" (ዮሐንስ ራዕይ 2፡10)

አሁን ማን ነው ጌታ ለራሱ ሰዎች ደንታ የለውም ያለው? የክርስትና ሕይወት ደስተኛ አይደለም ያለው ማንነው? የክርስትና ሕይወት ምንም የሚያመጣው የለም ያለው ማንነው? ክርስቲያን ሕይወት አንድ ሰው ሊኖረው የሚችለው ከሁሉ የተሻለን ነው፣ እጅግ የሚክስ ህይወት ነው፣ ስለዚህ አንድ ሰው ከኃጥያቱ ነፃ ወጥቶአል ጥሩ እና ሰላማዊ ህይወት ይመራል፣ እናም ለመኖር እና የሚጠብቀው ነገር ሁሉ አለው፡፡ በቁሳዊም በመንፈሳዊም የተባረከ ነው፡፡ ይህ ሁሉ የሚጀምረው ለወንጌል ሲታዘዝ ነው፣ ይህ በእውነቱ የህይወት መጀመሪያ ነው፣ ይህ የበረከት የመጀመሪያ ያልተገደበ ነው፡፡

## ጥያቄዎች

1. የጌታን የወንጌል በረከት የሚቀበሉ እነማን ናቸው?
2. ኤፌሶን 1፡3 አንብቡና ተወያዩበት
3. የክርስቶስን ወንጌል በመታዘዝ ምን እንቀበላለን ?

4. አንድ ሰው ወደ ክርስቶስ የሚገባው እንዴት ነው?
5. ይህን የሚደግፍ የተወሰኑ ጥቅሶች ስጥ
6. ሁሉም በረከቶች የት ነው የሚገኙት?
7. አንድ ሰው ወደ ቤተክርስቲያን የሚገባው በምን መንገድ ነው?
8. የክርስቶስ አካልን ግለፅ
9. በዓለም ላይ ትልቁ ተቋም ምንድነው? ለምን ትልቅ ሆነ?
10. 1ኛ ጴጥሮስ 4፡16 ጥቀስ
11. መዳን በማን ስም ነው?
12. ጌታ እንዴት የሚያመልኩትን ይሻል?
13. ለምንድነው መሰባሰባችንን እንዳንተው ያስጠነቀቀን?
14. በአምልኮአችን ላይ ትልቁና የተከበረው እንግዳ ማን ነው?
15. የኅብረት አስፈላጊነትን ግለፅ
16. ጌታ የኃጥያተኞችን ፀሎት ይሰማል?
17. ፀሎት የተሰጠው ለነማን ነው?
18. እንዴት ነው የምንፀልየው?
19. የጌታ እራትን ዓላማ ዘርዝር
20. እያንዳንዱ ክርስቲያን ሲታዘዝ የሚቀበለው ምንድነው?
21. በህይወታችን በመጀመሪያ ልናስቀድም የሚገባን ማን ነው?
22. በምን መልኩ ስንባረክ ነው ሌሎችን ልናስተምር የምንችለው?
23. የህይወትን አክሊል ጌታ የሚሰጠው ለነማን ነው?
24. ክርስቲያን መሆን ዋጋ አለው?

## ትምህርት አሥራ አንድ
## ወንጌልን መስበክ

ክርስቶስ እንዲህ አለ “እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችዋቸው ያዘዝኳችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችዋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው፣ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስብሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ”(ማቴዎስ 28፡19~20)፣ “እንዲህም አላቸው “ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ያመነ የተጠመቀም ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል” (ማርቆስ 16፡15~16)

ከነዝህ ጥቅሶች፣ የነገሮችን እውነት እንመልከት

1. ኢየሱስ ሐዋሪያቶችን አዝዞአል

ጌታ እንዲሄዱ ብቻ አልነገራቸውም ነገር ግን ዬት እንደሚሄዱም ነው የነገራቸው፡፡ ያላቸው ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፣ ወደ አህዛብ ሁሉ ሂዱ ወደ ፍጥረት በሙሉ ሂዱ ነው ያላቸው፡፡ ይህ ሁሉንም ፍጥረት ይመለከታል፣ ማንም ችላ ተብሎ የሚታለፍ የለም፡፡ ለዚያ ቀን እንኳን አሁን የምንጠቀምበት የመጓጓዣ ዘዴ የመገናኛ ሲስተም እንኳን ባልነበረበት ጊዜ ውስጥ ነበር ሆኖም ግን ጌታ መመሪያ

ሲሰጥ የማይቻለውን ሳይሆን የሚቻለውን ነውና ተቀበሉት አደረጉትም፡፡

2. ኢየሱስ ሂደው እንዲሰብኩ አዘዛቸው

እንዲሰብኩ ሲነግራቸው በግልፅ ምን እንደሚሰብኩ ነግሮአቸዋል፡፡ ያላቸው የሚሰበከው ወንጌል ነው አላቸው፣ አስተውል በዚህ ት ዕዛዝ ውስጥ ምንም ግራ መጋባት ወይም ግልፅ ያልሆነ ነገር የለም፣ ያመነ የተጠመቀም ይድናል፣ ያላመነ ይፈረድበታል" ብሏል (ማርቆስ 16፡16)

3. ኢየሱስ ለሐዋሪያቶች የሚያምኑትን ወንጌል የሚታዘዙትን እንዲያጠምቁ አዟቸዋል

በመጀመሪያ ደረጃ ማወቅ ያለብን ጌታ ለሐዋሪያቶቹ ወንጌልን ይዘው ወደ ዓለም ሁሉ እንዲሄዱ ኃላፍነትን ሰጥቶአቸዋል፣ ያም መፍትሔው ወንጌልን ለሁሉም እንዲሰበክ ማድረግ ነው፡፡ ነገር ግን ወንጌል ከተሰበከ ቦኃላ እና ወንጌልን ለመታዘዝ የሚፈቅዱ ሲኖሩ እንዲያጠምቋቸው ተናገረ እንዲህም አላቸው "በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችዋቸው" አለ (ማቴዎስ 28፡19) ስለዚህ በዚህ ላይ ለመረዳት የሚያስቸግር ነገር የለም፡፡

4. መጨረሻ ኢየሱስ ያስተማረው ወንጌል የታዘዙትን እንዲያስተምሯቸው ነው

ዳግመኛ ወደ ዓለም ሁሉ ሄደው ወንጌልን እንዲሰብኩና ከዚያም ለጌታ መታዘዝ የሚፈልጉትን እንዲያጠምቁ የጌታ ትዕዛዝ እንደሆነ አስተውል፡፡ አሁን ግን አንድ ጊዜ ይህ ከተደረገ ቦኃላ ሌላ ኃላፍነት ሰጣቸው ይህም በኢየሱስ ቃል ውስጥ ነው እንዲህ ይላል"እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" (ማቴዎስ 28፡20) ይህም ማለት ጌታ ወደ የትኛውም አቅጣጫ ቢሄዱ ሁኔታውን ለማስተካከል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም በመጀመሪያዎቹ የወንጌል መርሆዎች የሚታዘዙ ሰዎች መንፈሳዊነታቸውን እንዲሞቱ ሳይሆን እንዲማሩ ለማድረግ አስቦአል፡፡ እና የክርስትና ህይወት ለመምራት መንገድን ተምረዋል፡፡ በዚህ መንገድ ለቅርብ ጊዜ መዳናቸው ብቻ ሳይሆን ለዘላለማዊ መዳናቸውም ፍላጎት አሳይቶአል፡፡ ታማኝ በሆነው ክርስቲያናዊ ህይወት ለመኖር እንዲዘጋጁ ፈልጎ ነበር ይህ ደግሞ ተጨማሪ ትምህርት በመስጠት ብቻ ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሰው በተለምዶ እንደታላቅ ተልዕኮ ተሰጥቶአል ይህም ወንጌልን የመስበክ ትዕዛዝ ዓለምን የሚያካትት እና መልዕክቱ በጣም ትልቅ እና ለነግስ መዳን አስፈላጊ ነው፡፡ ነገር ግን በመቀጠል ጌታ ይህ ተልዕኮ እንዲፈፀም እንዴት እንዳቀደ ማየት እንፈልጋለን ወደ ሐዋሪያ *ሥራ* 1፡8 ስንሸጋገር የጌታን እቅድ ወደ ተከታታይ ጅኦግራፊያዊ ደረጃዎች አወርዋል ለሐዋሪያት ሲናገር እንዲህ አለ "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፣ በኢየሩሳለምም በይሁዳም ሁሉ በሰማሪያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ" (ሐዋሪያ *ሥራ* 1፡8) የሐዋሪያ *ሥራ* መፅሐፍን በምናነብበት ጊዜ እነዚህ ነገሮች ተከስተው እናገኛለን

1. ወንጌል ከኢየሩሳለም ጀምሮ ተሰብኮአል
የሐዋሪያት ሥራ 1 እና 2 ስናነብ የምናገኘው ፦ ሐዋሪያቶች በኢየሩሣሌም ነበሩ፣የጴንጤቆስጤ ቀን መጣ፣ከዓለም ዙሪያ አይሁዶች ተሰበሰቡ፣ ከዚያ መንፈስ ቅዱስ በሐዋሪያቶች ላይ ፈሰሰና እዚያ ባሉት ሰዎች ሁሉ ቋንቋ መናገር ጀመሩ፣ ከዚያም ወንጌልን ለመጀመሪያ ጊዜ በዚያ ቦታ ሰበኩ፣ በዚያ ስብከት ውጤት ሦስት ሺህ የሚሆኑ ነፍሳት ተጠመቁ በቤተክርስቲያን ላይ ተጨመሩ፣ ከዚህ በመነሳት ነው ወንጌል በሁሉም ቦታ መሰራጨት የጀመረው፡፡ በዚህ ጊዜ ሰዎች ከመላው ዓለም በተሰበሰቡበት ወንጌል እንዲሰበክ በማድረጉ በጌታ ጥበብ፣ ከነዚህም መካከል ልዩ ልዩ ጌታን በመታዘዝ ወንጌል ስርጭት መጀመሩን ያመለክታል፡፡ ጉዳዩን ለውገኖቻቸው ለመንገር ወደ ሀገራቸው ተመልሰው እንዲሰራጭ አድርገዋል፡፡ ለምሣሌ፣ ከሮም የመጡ እንግዶች መገኘታቸውን እናነባለን ከዚያም ጳውሎስ እዚያ ከመጎብኘቱ በፊት በሮም ስላለች ቤተክርስቲያን እናነባለን እናም ቅዱሳት መፅሐፍት ጴጥሮስ ወደዚያ እንደሄደ ወይም ከሌሎች ሐዋሪያት መካከል አንዳቸውም ከዚያ በፊት እንደሄዱ አይናገርም፡፡ ታዲያ ማብራሪያው ምንድነው? በግልፅ ለማየት እንደሚቻለው እነዚህ ከሮም የመጡ እንግዶች ለውንጌል ታዘዙ፣ ወደ ቤታቸው ተመልሰው የራሳቸውን ህዝብ አስተምረዋል፣ በዚህም ቤተክርስቲያን ተመስርታለች፡፡

2. ወንጌል በመላው ይሁዳ ተሰበከ
ይሁዳም ወዲያው በኢየሩሣሌም አከባቢ በዚያ ነበረች፣ ይህ ማለት በዚያን ጊዜ የዚህን ክስተት ለመስበክ ችግር አልነበረባቸውም ማለት ነው፡፡ ስለዚህም በቀጣዮቹ ቀናት ወንጌል በኢየሩሣሌምና በይሁዳ ተሰበከ፡፡ ከዚያም ስለ እስጥፋኖስ ሞት እናነባለን "በዚያን ቀንም በኢየሩሳለም ባለች ቤተክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ሆነ፣ ሁሉም ከሐዋሪያት በቀር ወደ ይሁዳና ወደ ሰማሪያ አገሮች ተበተኑ" (የሐዋሪያት ሥራ 8፡1)፣ ስለነዚህ የተበተኑትን ማንበብ ስንቀጥል "የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ" (የሐዋሪያት ሥራ 8፡4)፣ ስለዚህ ወንጌል በመላው ይሁዳ ተሰበከ፡፡

3. ወንጌል ወደ ሰማሪያ ሰዎች ተወሰደ
"ፊሊጶስም ወደ ሰማሪያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው፣ ህዝቡም የፊሊጶስን ቃል በሰሙ ጊዜ ያደርጋት የነበረውንም ምልክት ባዩ ጊዜ የተናገረውን በአንድ ልብ አደመጡ" የሐዋሪያት ሥራ 8፡5~6)፣ "ነገር ግን ስለእግዚአብሄር መንግሥትና ስለኢየሱስ ክርስቶስ ስም እየሰበከላቸው ፊሊጶስን ባመኑት ጊዜ ወንዶቻም ሴቶቸም ተጠመቁ" (የሐዋሪያት ሥራ 8፡12)፣ በኋላ ዮሐንስና ጴጥሮስ ሊጎበኟቸው ሲሄዱ የሆነውን ዘገባው ሲነግረን "እነርሱም ከመሰከሩና የጌታን ቃል ከተናገሩ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፣ በሳምራዊያን በብዙ መንደሮቸም ወንጌልን ሰበኩ" (የሐዋሪያት ሥራ 8፡25)፣ ስለዚህ እንደ ጌታ እቅድ ሰማሪያም ወንጌልን ሰሙ፡፡

4. በመጨረሻም ወንጌል ወደ መላው ዓለም ተወሰደ

ወንጌል ወደ መላው ዓለም መወሰዱን ለማረጋገጥ፣ ጳውሎስ እንዲህ ይላል “ይህም ተመስርታችሁና ተደላድላችሁ ከሰማችሁትም ከወንጌል ተስፋ ሳትናወጡ በሃይማኖት ፀንታችሁ ብትኖሩ ይሆናል፣ ያም ወንጌል ከሰማይ በታች ባለው ፍጥረት ሁሉ ዘንድ የተሰበከ ነው፣ እኔም ጳውሎስ የእርሱ አገልጋይ ሆንሁ” ይላል (ቆላስያስ 1፡23)፣ ስለዚህ የጌታ እቅድ ዓለም ሙሉ በሙሉ በሰላሳ ዓመት ውስጥ አጥለቅልቋል፡፡

አሁን ጌታ እኛን ምን እንድናደርግ ይፈልጋል? ተመሳሳይ ነገር እንድናደርግ ይፈልጋል፡፡ ይህ ነው እንግዲህ፣ እኛም ወንጌልን በተመሳሳይ መልኩ ለዓለም ሁሉ ልናደርስ ይጠበቅብናል፣ ለሁሉ ፍጥረት፣ ለሁሉ ሕዝብ ለዓለም ሁሉ ንፁሁን ወንጌል ማድረስ ይገባናል፡፡ ብዙ ንፁህን ወንጌል ያልሰሙ ስላሉ ትልቅ ሥራ አለብን ነገር ግን በእጃችን ያሉትን ዘመናዊ መገልገያዎችን ለምሣሌ እንደ መጓጓዣ ግንኙነት ወዘተ ስናስብ ሥራችን ቀላል ሆኖ ይታያል፡፡ ጌታም የማይቻለውን አይጠይቀንም፡፡

ለዓለም የክርስቶስ ወንጌል ያስፈልጋታል፣ይህ ወንጌል ለዓለም ተስፋዋ ነው፣ ዓለምን ሊቀይር ሊለውጥ የሚችለው ብቸኛው ወንጌል ብቻ ነው፣ ሊረዳት የሚችል ወንጌል ብቻ ነው፣ ሊያድናት የሚችል ወንጌል ብቻ ነው፣ ስለዚህ ይህን ወንጌል የያዝን እኛ ይህንን ጉዳይ አይተናልና ለዓለም ሁሉ ልንሰብክ ይገባናል፡፡

## ጥያቄዎች

1. ማቴዎስ 28፡19~20 እና ማርቆስ 16፡15~16 አንብቡና ተውያዩበት
2. ጌታ ማንን ነው እንዲሄዱ ያዘዘው?
3. ዬት ነው እንዲሄዱ ያዘዘው?
4. ጌታ የማይቻለውን ይጠይቃል?
5. ምን እንዲሰብኩ ነው ያዘዛቸው?
6. ማንን ነው ሐዋሪያቶች የሚያጠምቁት?
7. በማን ስም ነው የሚያጠምቁት?
8. የተጠመቁትን እንዲያስተምሩ የታዘዙት ምንን ነው?
9. ለምንድነው ማቴዎስ 28፡19~20 እና ማርቆስ 16፡15~16 ታላቁ ትዕዛዝ የተባለው?
10. የሐዋሪያት ሥራ 1፡8 ጥቀስ
11. ለወንገል ስርጭት የተጠቀሰውን ጂኦግራፋዊ ድረጃ ጥቀስ
12. ዬት ነው የወንጌል ስብከት የተጀመረው?
13. በሐዋሪያ ሥራ 2 ላይ የተከሰተውን ተወያዩበት
14. ከመጀመሪያው ጀምሮ ወንጌል በዓለም ሁሉ እንዲዳረስ እንዴት ተቻለ?
15. በመላ ይሁዳ ወንጌል ማዳረስ እንዲቻል ማን አደረገ?
16. ወደ ሰማሪያ ወንጌልን የወሰደ ማንነው?
17. ወንጌል ወደ ዓለም ሁሉ ደርሷል? ማንነው ያለው? ዬት ቦታ?

18. የእኛ የዛሬ ሥራ ምን መሆን አለበት?
19. ማድረግ እንችላለን?
20. እስቲ በዛሬው ዕለት የተመቻቹ የመገልገያ መሣሪያዎችን ጥቀስ
21. አሁንም ዓ፤እ ወንጌል ያስፈልጋታል? ለምን ?

## ትምህርት አሥራ ሁለት
## ሌላ ወንጌል መስበክ

አዲስ ኪዳን የኢየሱስ ክርስቶስን አንድ ወንጌል መስበክ አስፈላጊ መሆኑን ሲያጎላ ስለ ሌላ ወንጌልም ይናገራል፡፡ ጳውሎስ ሲስጠነቅቅ እንዲህ ይላል "የሚመጣውም ያልሰበክነውን ሌላ አየሱስ ቢሰብክ፣ ወይም ያላገኛችሁትን ልዩ መንፈስ ወይም ያልተቀበላችሁትን ልዩ ወንጌል ብታገኙ በመልካም ትታገሱታላችሁ" (2ኛ ቆሮንቶስ 11፡4)፣ ከዚህም ቀጥሎ ደግሞ እንዲህ ይላል፣ "እንደነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋሪያት እንዲመስሉ ራሳቸውን እየለወጡ ውሸተኞች ሐዋሪያትና ተንኮለኞች ሠራተኞች ናቸውና ይህም ድንቅ አይደለም፣ ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልዓክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና እንግዲህ አገልጋዮቹ ደግሞ የፅድቅን አገልጋዮች እንዲመስሉ ራሳቸውን ቢለውጡ ታላቅ ነገር አይደለም፣ ፊፃሜያቸውም እንደሥራቸው ይሆናል" (2ቆሮንቶስ 11፡13~15)

ጳውሎስ ለገላቲያ ሲፅፍ እንዲህ ይላል ፦ "በክርስቶስ ፀጋ እናንተን ከጠራችሁ ከእርሱ ወደ ልዩ ወንጌል እንዲህ ፈጥናችሁ እንዴት እንዳለፋችሁ እደነቃለሁ እርሱ ግን ሌላ ወንጌል አይደለም፣ የሚያናውጧችሁ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ አንዳንዶች አሉ እንጂ ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፣ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ፣ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን" ይላል (ገላቲያ 1፡6~9) አሁን ሐዋሪያው ምን እያለ ነው? የሚከተለውን እናስተውል፦

1. የገላቲያ ሰዎች ንፁህ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ተቀብለው ነበር፦
2. ጳውሎስ ብዙም ሳይቆይ ወደ ሌላ ወንጌል መዞራቸውን አይቶ ተገረመ፡፡ ነገር ግን ንፁህ ወንጌል በመሆን ሌላ ወንጌል እንዳልሆነ ያስረዳል፡፡
3. ከእነርሱም መካከል የክርስቶስን ወንጌል ከንቱ የሚያደርጉ የሚያጣምሙ ወይም የሚቀይሩ አሉ
4. ከዚያም ጳውሎስ ራሱን ጨምሮ እሱ እና ሌሎች ወይም ከሰማይ የመጣ መልአክ፣ ምንም እንኳን አስቀድሞ ከተሰበከው ወንጌል ውጭ ሌላ ወንጌል ቢሰብክላቸው፣ በዚያን ጊዜ በእግዚአብሄር የተረገሙ እንደሚሆኑ ሲናገር ይህ ማለት ንፁህ ወንጌል አስቀድሞ ተሰብኮ ነበር እና የሚሰበከውም ሁሉ ንፁህ ወንጌል ሊሆን አይችልም ማለት ነው፡፡ እነዚህ የተለየ ወንጌል የሚሰብኩት እርግማን ሲያገኛቸው የጌታን ንፁህ ወንጌል የሚሰብከውን ግን የጌታ በረከት በእርሱ ላይ

ያርፋል ውጤቱንም ይቀበላል፡፡

5. ጳውሎስ በማስጠንቀቂያው ላይ አፅናኦት ለመስጠት ራሱን ደግሟል

አሁን ከላይ ከተመለከትነው የጌታ እቅድ ሌላ ወንጌልን ለማንሳት ምንም ቦታ እንደሌለው እንጂ ወንጌላትን መጥቀስ አይደለም፡፡ በእግዚአብሄር ቃል ውስጥ ለምናነበው ወንጌል የእግዚአብሄር እርግማን በሚያደርጉት ላይ ይወርዳልና፡፡ ለምን ? ምክንያቱም ጌታ ለማንም ሰው ሌላ ወንጌል እንዲሰብክ መብትም ሥልጣንም አልሰጠውም ሌላ ወንጌል መስበክ ማለት ንፁሁን የክርስቶስን ወንጌል ጥሏል ማለት ነውና፡፡

ከላይ የተገለፀው ነገር ቢኖርም በዛሬው ጊዜ ብዙ ወንጌሎች እየተሰበኩ እንዳሉ እናውቃለን፡፡ ይሄውም ብዙ የደህንነት እቅዶች፣ ተቃራኒ ትምህርቶች፣ ወዘተ እየተሰበኩ ነው፡፡ ንፁህ ወንጌል ዬትኛው ነው? ትክክለኛው ወንጌል እንዳለን እንዴት እናውቃለን ? እስቲ እነዚህን አስተውሏቸው

1. ስለ ወንጌል እውነት ወደ መፅሐፍ ቅዱስ ተመለስ፣ የእግዚአብሄር መፅሐፍ የክርስቶስን ምሥራች በተመለከተ የእውነት ምንጭ ነው፡፡ በገፆቹ ላይ ስለ ወንጌል እውነታዎች ማንበብ ትችላለህ (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡1~4)፣ እና ትዕዛዛት (ማርቆስ 16፡15~16፣ የሐዋሪያ ሥራ 2፡38) እነዚህን የእግዚአብሄርን ቃል በማጥናት እሱ የሚናገረህን በማድረግ ጥርጣሬህን ግራ መጋባትህን እና ጥያቄዎችህን ማስወገድ ትችላለህ/

2. ከቅዱሳት መፅሐፍት ትምህርት ጋር የሚጋጭ ዬትኛውንም የወንጌል የድነት እቅድ ላይ ያለውን ትምህርት ውድቅ አድርግ፡፡ ሰው በዚህ ርዕስ ጉዳይ ላይ የራሱን አማራጮች እና አስተሳሰቦች የማቅረብ ሥልጣን አልተሰጠውም እና ማንም ትክክለኛ አስተሳሰብ ያለው ሰው አይቀበላቸውም

3. የሐይማኖት ድርጅት ሰባኪዎች የሚያውጁት እነዚህ ወንጌሎች ንፁህ የመፅሐፍ ቅዱስ ወንጌል ሊሆን አይችሉም፡፡ ለክርስቶስ ወንጌል መታዘዝ ወደ ሐይማኖት ድርጅት ቤተ እምነት አያስገባህም እና ሰው ሰው ሰራሽ ስም ወይም ማዕረግ እንድትለብስ አያደርግህም ይህን በአዕምሮህ አስብ፣ ይልቁንም የክርስቶስን ወንጌል መታዘዝ ውጤቱ ለናንተ መዳን ይሆንላችዋል እናም ወደ ጌታ ቤተክርስቲያን የመጨመር እና በዚህም እርስዎ ክርስቲያን ብቻ ያደርጋችዋል እንጂ ሌላ ስያሜ አያሰጣችሁም፡፡ እባክዎትን ሐዋሪያ ሥራ 2፡38፣ 47፣ ሐዋሪያ ሥራ 11፡ 26 አንብቡ፡፡

4. ያለ ጥምቀት መዳን ይቻላል ብለው “እምነትን ብቻ” የሚያስተምሩትን ተጠንቀቁ፣ እና የመሳሰሉትን ተጠንቀቁ፣ እነዚህ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካነበብነው ይልቅ ሌሎች ወንጌልን የሚሰብኩ ሰዎች የሚያስተምሩት ለሰው አዕምሮ ተወዳጅ ትምህርቶች ናቸው እናም ይህ የጳውሎስ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው መፅሐፍ ቅዱስ ሰው እንዲድን ማመን ብቻ ሳይሆን እርሱ ደግሞ መጠመቅ እንዳለበት ስለሚያስተምር ነው (ማርቆስ 16፡16)፡፡

5. አብዛኞቹ ወደ ጥፋት በሚወስደው ሰፊ መንገድ ላይ እንዳሉ አስታውስ

(ማቴዎስ 7፡13~14) አንዳንድ ጊዜ ሌሎች ወንጌሎችን የሚሰብኩ ሰዎች በእነዚህ ነገሮች ስለሚያምኑ ተጎጂዎቻቸውን ይማርካሉ፣ ምንም እንኳን ብዙ ቢሆኑም ብዙዎቹ ስህተት እንደሆኑ ያስታውሱ።

6. ዛሬ እየተሰበኩ ያሉት እነዚህ አዳዲስ እና ዘመናዊ ወንጌሎች መለያየትን ያመለክታሉ። መከፋፈልን ያበረታታሉ፣ መለያየትን በግልፅ ይሰብካሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል አንድነትን፣ ኅብረትንና ሰላምን ያበረታታል 1ኛ ቆሮንቶስ 1 እና 1ኛ ቆሮንቶስ 12 አንብብ ፣ ከዚያም በዮሐንስ 17 ላይ ጌታ ሐዋሪያት አንድ እንዲሆኑ እንዴት እንደፀለየ እና ትምህርታቸውን የሚያምኑ ሁሉ አንድ እንዲሆኑ መፀለዩን አንብብ።

7. በመጨረሻም እነዚህ ሌሎች ወንጌሎች እንደማያድኑ አስታውስ፣ ይልቁንም የሚሰብኩትንም የሚቀበሉትንም እንዲጠፉ ያደርጋል፣ የማዳን ኃይል ያለው የክርስቶስ ወንጌል ብቻ ነው፣ (ሮሜ 1፡16~17)።

መለያየት የሚፈጠረው በስህተት ስብከት ወይም በስህተት ትምህርት ነው። ስለዚህም ጳውሎስ አስጠንቅቆአል "ነገር ግን ወንድሞች ሆይ፣ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትንና ፣አሰናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችዋለሁ ከእነርሱ ፈቀቅ በሉ፣ እንዲህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና በመልካምና በሚያቆላምጥ ንግግርም ተንኮል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ" (ሮሜ 16፡ 17~18) በዚህ መሰረት እንደዚህ ዓይነት ሰባኪዎችን ምልክት ልናደርግላቸው ይገባል እና እነሱም መወገድ አለባቸው ዮሐንስ ሲፅፍ "ለሚወጣ ሁሉ በክርስቶስም ትምህርት ለማይኖር ሰው አምላክ የለውም፣ በክርስቶስ ትምህርት ለሚኖር አብና ወልድ አሉት ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይህንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት ሠላምም አትበሉት ሰላም የሚለው ሰው በክፉ ሥራው ይካፈላልና" (2ኛ ዮሐንስ 9~11)፣ ከዚያም ክርስቶስ ራሱ አስጠንቅቋል "በዚህ መፅሐፍ የተፃፈውን የትንቢት ቃል ለሚሰማ ሁሉ እኔ እመሰክራለሁ ማንም በዚህ ላይ አንዳች ቢጨምር እግዚአብሄር በዚህ መፅሐፍ የተፃፉትን መቅሰፍቶች እጨምርበታል ማንምም በዚህ በትንቢት መፅሐፍ ከተፃፉት ቃሎች አንዳች ቢያጎድል በዚህ መፅሐፍ ከተፃፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሄር ዕድሉን ያጎድልበታል" (ዮሐንስ ራዕይ 22፡18~19)

አሁን ሌሎች ወንጌሎችን ከሚሰብኩ ሰዎች መካከል ብዙዎቹ በሚያስተምሩት ነገር ሀቀኛና ቅን ናቸው። እነሱ በቀላሉ ተታለዋል እንገር ግን ስህተትን እያስተማሩ መሆናቸውን አያስወግዱውም እና ስለዚህ አሁንም ለእግዚአብሄር መልስ መስጠት አለባቸው። ሌሎች ግን ሐቀኛና ቅን አይደሉም እነዚህ በተለይ ስለሚቀጠሩ ሰዎች ነው እውነቱን ያውቀዋል ስለሚከፈለው ብቻ መተዳደሪያ ስለሆነ ብቻ ለነፍሳት ደንታ የለውም። ደሞዙን እስካገኘ ድረስ ምንም ይሁን ምን ያልሆነውን ይዋሻል። ያም ሆነ ይህ በእነዚህ ሁሉ አትታለሉ።

የሐይማኖት ድርጅት ቡድኖች ዛሬ ስለ አንድነት ብዙ እያወሩ ነው። ያም

ሆኖ ግን እየከፋፈሉ ይገኛሉ፣ ነገር ግን በእውነት አንድነትን የሚፈልጉ ከሆነ ሁሉም ወደ መፅሐፍ ቅዱስ ለአንድ ወንጌል ይመለሱ፣ እሱን ወንጌል ብቻ ይስበኩና አንድነት ውጤቱ ይሆናል። ያ ቀላል ነው።

## ጥያቄዎች

1. ከአንድ ሌላ ንፁህ ወንጌል አለ?
2. 2ኛ ቆሮንቶስ 11፡4 2ኛ ቆሮንቶስ 11፡13~15 እና ገላቲያን 1፡6~9 አንብብ
3. ለገላቲያኖች ማንነው የሰበከው?
4. ወደ ምን ዓይነት ወንጌል ነው የተመለሱት?
5. የተለየ ወንጌል በሚሰብኩት ላይ ምን ይመጣል?
6. ዛሬም እንደዚያ ዓይነት ሌላ ወንጌል ይሰበካል?
7. ዬትኛው ነው ንፁህ የክርስቶስ ወንጌል?
8. የክርስቶስ ትክክለኛ ወንጌል ለማወቅ ወደ ዬትኛው መፅሐፍ መሄድ አለብን?
9. ከቅዱሳት መፅሐፍት ጋር የሚጋጭ ከሆነ ዬትኛውም ትምህርት እውነትን ሊወክል ይችላል?
10. ሰዎች የራሳቸውን ሀሳብ ወይም አስተያየት መጨመር ሥልጣን አላቸው?
11. ለእነዚህ የሐይማኖት ድርጅት ሰባኪዎች የክርስጽን ወንጌል መስበክ ይቻላቸዋል?
12. በክርስቶስ ወንጌል አምኖ መታዘዝ ወደ ሐይማኖት ድርጅት ይጨምራል?
13. በመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርት ንፁህ ወንጌል ሲታዘዙ ውጤቱ ምን ይሆናል?
14. እምነትን ብቻ የሚሰብክ ማንነው?
15. ብዙዎቹ በምን ዓይነት መንገድ ላይ ናቸው?
16. የዘመናችን አዳዲስ ወንጌሎች ምንን ያመለክታሉ?
17. የክርስቶስ ወንጌል ምን ያስተምራል?
18. ሌሎቹ ወንጌሎች ያድናሉ?
19. እንዴት ነው መለያየት የሚመጣው?
20. ሮሜ 16፡17~18፣ 2ኛ ዮሐንስ 9~11፣ እና ዮሐንስ ራዕይ 22፡18~19 አንብብ
21. እነዚህ ሌላ ወንጌል የሚሰብኩት በሚያደርጉት  ነገር ላይ ታማኞች ናቸው?
22. ተቀጥረው የሚሰብኩጽ ?
23. እንዴት ነው በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ ያለው አንድነት ሊመጣ የሚችለው?

## ትምህርት አሥራ ሦስት
## ወንጌልን ማደናቀፍ

ጳውሎስ ወንጌልን የሚሰብኩ ሰዎች በወንጌል እንዲኖሩ ወይም ድጋፍ እንዲኖራቸው ስለመሆኑ ሲወያይ እንዲ ይላል "ሌሎች በእናንተ ላይ ይህን መብት የሚካፈሉ ከሆኑ እኛማ ይልቁን እንዴታ? ነገር ግን የክርስቶስን ወንጌል እንዳንከለክል በሁሉ እንታገሳለን እንጂ በዚህ መብት አልተጠቀምንም" (1ኛ ቆሮንቶስ 9፡12)፣ ምንም እንኳን ወንጌልን ባይከለክልም እሱ ወይም ሌላ ሰው ይህን ማድረግ እንደሚችል በእርግጠኝነት ያውቃል። ዛሬም ቢሆን ተመሳሳይ ነው።

በተፈጥሮ ስህተትን የሚሰብኩ እና ስህተትን የሚያራምዱ ሰዎች የክርስቶስን ወንጌል ለማደናቀፍ ብዙ ያደርጋሉ፣ ይህ እውነት ካልሆነ በጣም ሩቅ የሆነውን ውጢት ያስቡ፣ በሌላ በኩል ምናልባት ብዙ ወይም ከዚያ በላይ ጉዳት የሚደርሰው በቤተክርስቲያን አባላት በራሳቸው ነው፣ እንግዲህ የክርስቶስን ወንጌል የምናደናቅፍባቸውን መንገዶች እናስብ።

1. የክርስቶስን ወንጌል ሳንሰብክ እና ለሌሎች ሳናስተምር እንቅፋት እንሆናለን፣ ወንጌል ለሁሉም ነው። ወደዚያ እንገባለን ጌታ ወደ ባለንጀሮቻችን እንድንወስደው አዘዘን (ማርቆስ 16፡16) አሁን ይህንን ለማድረግ ሁለት መንገዶች አሉ። በአፍ ልንሰብከው ወይም በምንኖርበት መንገድ ልናስተምረው እንችላለን። ሁሉንም መደረግ አለበት ከሁለቱም አንዳንዶቹ ይሠራሉ ብዙዎቹ በሁለቱም ይሠራሉ ይህም ማለት ወንጌልን ለሌሎች ማድረስ ሲያቅተን ግስጋሴውን እያደናቀፍን ነው ማለት ነው። ይህ ኃጥያት ነው።

2. በአምልኮ ላይ የማንገኝ ከሆነ ለወንጌል እንቅፋት ይሆናል። እንዴት? በጣም ቀላል ነው ወደ አምልኮ ካልሄድን እኛ ራሳችን ጌታን ማምለክ አለመቻላችን ብቻ ሳይሆን ከጌታ መቀበል የሚገባንን መንፈሳዊ ምግብ ማግኘት ይሳነናል። ከዚህ ባለፈ ግን ለሌሎች ተገቢውን አርአያ መሆን እና በአርአያነት ወንጌልን ማስተማር ከሚያስፈልጋቸው ሰዎች ጋር በመገናኘት የኛ የሆነውን ዕድል መጠቀም ተስኖናል ማለትም ነው። ይህንን የዕብራዊያን ፀሐፊ ሲጠቅስ "የተስፋን ቃል የሰጠ የታመነ ነውና እንዳይነቃነቅ የተስፋችንን ምስክርነት እንጠብቅ፣ ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ፣ በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደሆነው መሰብሰባችንን አንተው እርስበርሳችን እንመካከር እንጂ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ፣ የእውነትን እውቀት ከተቀበልን ቦኃላ ወደን ኃጥያት ብናደርግ ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ኃጥያት ምሥዋዕት አይቀርልንምና የሚይስፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ ተቃዋሚዎቸንም ሊበላ ያለው የእሳት ብርታት አለ" (ዕብራዊያን 10፡23~27)

3. እንደ ክርስቲያን ማደግ ሲያቅተን ወንጌልን እንገድባለን፣ መንፈሳችን ደካማ ሲሆን ሌሎችን ከማስተማር ይልቅ የሚያስተምረን እንፈልገናል። የዕብራዊያን ፀሐፊ የሚናገረው ይህንን ነው "ከጊዜው የተነሣ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ፣ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሄር ቃላት መጀመሪያ ያለውን

የሕፃንነትን ትምህርት እንዲያስተምራቸሁ እንደገና ያስፈልጋቸዋልና፣ የሚይስፈልጋቸሁም ወተት ነው እንጂ ጠንካራ ምግብ አይደለም፣ ወተት የሚጋት ሁሉ ሕፃን ስለሆነ የፅድቅን ቃል አያውቅምና፣ ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙንና ክፉውን ለመለየት በሥራቸው የለመደ ልቡና ላላቸው ለፊፁማን ሰዎቸ ነው” (ዕብራዊያን 5፡12~14)

4. እንደሚገባን መኖር ሲያቅተን የጌታን ጉዳይ እናደናቅፋለን፣ በዚህ ሁኔታ በጌታ ስም ላይ እፍረት እናመጣለን፡፡ ዓለም የንቀት ጣት ወደ እኛ እየቀሰረ ክርስትናን የሚወክል ከሆነ የሱን ክፍል አልፈልግም ይላል፡፡ ጥሩ እና ቅን ሰዎቸ እንዲሰናከሉ እናደርጋቸዋለን ሌሎቸ እንዲከተሉት መጥፎ ምሣሌ እንሆናለን፡፡ ይህ ሁሉ ያማል፡፡ ጌታ ክርቲያን የሚለውን ስም እንድንለብስ ብቻ ሳይሆን በእውነት ክርስቲያን እንድንሆን ይፈልጋል ሁሉን በስሙ ለክብሩ እንድናደርግ ይፈልጋል፣ ጳውሎስን አድምጥ “እግዚአብሄር አብን በእርሱ እያመሰገናቸሁ፣ በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት” ይላል (ቆላስያስ 3፡17)፣ እንደዚሁም ሐዋሪያው ጴጥሮስ ሲያበረታታቸው “ ስለክርስቶስ ስም ብትነቀፉ የክብር መንፈስ የእግዚአብሄር መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፉልና ብፁዓን ናቸሁ፣ ከእናንተ ማንም ነፍሰ ገዳይ ወይም ሌባ ወይም ክፉ አድራጊ እንደሚሆን ወይም በሌሎቸ ጉዳይ እንደሚገባ ሆኖ መከራን አይቀበል ክርስቲያን እንደሚሆን ግን መከራን ቢቀበል ስለዚህ ስም እግዚአብሄርን ያመስግን እንጂ አይፈር፣ ፍርድ ከእግዚአብሄር ቤት ተነስቶ የሚጀምርበት ገዜ ደርሷልና፣ አስቀድሞም በእኛ የሚጀመር ከሆነ ለእግዚአብሄር ወንጌል የማይታዘዙ መጨረሻቸው ምን ይሆን? ደግሞም በጭንቅ የሚድን ከሆነ ዓመፀኛውና ኃጥያተኛው ወዴት ይታይ ዘንድ አለው? ስለዚህ ደግሞ እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ መከራን የሚቀበሉ፣ መልካምን እያደረጉ ነፍሳቸውን ለታመነ ፈጣሪ አደራ ይስጡ” ይላል (1ኛ ጴጥሮስ 4፡14~19)

5. ግዴታቸንን እና ኃላፊነታቸንን በመተው የጌታን ሥራ እንቅፋት ልንሆን እንቸላለን፡፡ መጥፎ ያልሆኑ ወይም ሥነ ምግባር የጎደላቸው ብዙ የቤተክርስቲያን አባላት አሉ፡፡ ሆነ ብለው እና ሆን ብለው መጥፎ ወይም ስህተት የሆነውን ነገር አያደርጉም፣ ሌሎቸ ደግሞ በጣም ጥሩ ሰዎቸ ናቸው ይላሉ ነገር ግን ደካማ ነጥባቸው ማድረግ የሚገባቸውን ብዙ ሥራዎቸን ወደ ጎን በመተው በቀላሉ መንሳፈፋቸው ነው፡፡ ነገር ግን ቸልተኝነት፣ እርምጃ አለመውሰድ፣ ግድ የለሽነት፣ ወዘተ አደገኛ ሊሆኑ ይቸላሉ፡፡ ይህ በእያንዳንዱ የዕለት ዕለት ህይወት ውስጥ እውነት እንደሆነ እናውቃለን፣ በመንፈሳዊው ዓለም እውነት ነው፣ ስለዚህም ነገር ያዕቆብ እንዲህ ይላል “ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳቸሁን እያሳታቸሁ የምጸሙ ብቻ አትሁኑ” ይላል (ያዕቆብ 1፡22) እንዲሁም ያኽቆብ 2 አንብብ ስለ እምነት ብቻ በእምነታቸው የሚሄዱት ምንም ስለሌላቸው ያዕቆብ 4፡ 17 ይገልታፃል፣ በመጨረሻም የምናነነበው “ስለዚህ ከሰማነው ነገር ምናልባት እንዳንወሰድ ለእርሱ አብልጠን ልንጠነቀቅ ያስፈልገናል፡፡ በመላእክት የተነገረው ቃል ፅኑ ከሆነ መተላለፍና አለመታዘዝም ሁሉ የፅድቅን ብድራት ከተቀበለ፣ እኛስ

እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል ብንለው፣ እንዴት እናመልጣለን? ይህ በጌታ በመጀመሪያ የተነገረ ነበርና የሰሙትም ለእኛ አፀኑት” (ዕብራዊያን 2፡1~3)።

6. ካገኘነው ለጌታ ሥራ ባለመስጠት የወንጌል እንቅፋት ልንሆን እንችላለን። ቤተክርስቲያን ድሆችን የመርዳት እና ወንጌልን በመስበክ ሥራዋን እንድትቀጥል ለማስቻል ምዕመናን በሚሰጡት አቅም ላይ የተመካ ነው። ነገር ግን አንሰጥም እንበል ። ይህ ማለት ግን ቤተክርስቲያን መዘከም አትችልም ማለት አይደለም ሌሎች አባላት ሊሰጡ ስለሚችሉ ይሁን እንጂ፣ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ያለች ቤተክርስቲያን ጥረቷ ውስን ይሆናል። ለዚህም ነው መፅሐፍ ቅዱስ መስጠት ተስንን አምላክን እየዘረፍን እንደሆነ ወይም እሱን እየገደብነው እንደሆነ የሚናገረው። የበለጠ እንዲሠራ ስንሰጠው የበለጠ ማድረግ ይችላል፣ ስለዚህም ጳውሎስ ሲመክር “እኔ ስመጣ ይህ ገንዘብ ማዋጣት ያን ጊዜ እንዳይሆን፣ ከእናንተ እያንዳንዱ በየሣምንቱ በፊተኛው ቀን እንደቀናው መጠን እያስቀረ በቤቱ ያስቀምጥ” (1ኛ ቆሮንቶስ 16፡2) የምንችለውን ያህል መስጠት ካልቻል አንድ ሰው ወንጌልን መስማት እንዳይችል ወይም የተቸገረ ሰው ያለ ምንም ሊደረግለት እንደማይችል እናስብ። ስለዚህ የራሳችንን ነፍስ ጨምሮ የተለያዩ ነፍሳት፣ እንዲሁም ሰዎች አካላዊ ደህንነት እንደሚሳተፉ ስንገነዘብ በጣም አሳሳቢ ጉዳይ ነው።

ስለዚህ ከላይ ከተገለፁት ነጥቦች መረዳት የምንችለው ሐይማኖታዊውን ዓለም በተለይም የእምነት ቡድኖች ለኣለም ወንጌልን መስበክ ባለመቻላችን ለውድቀታችን  ተጠያቂ ቢሆኑም አብዛኛው ጥፋቱ ግን  በእግራችን ሥር ነው። በእርግጥ እነዚህ ሐይማኖታዊ ድርጅት የንፁህ የአዲስ ኪዳን ክርስትናን መስፋፋት ሊያደናቅፉ ይችላሉ ነገር ግን እኛ መሆን ያለብን እስከሆንን ድረስ እና ጌታ የሚፈልገውን እስካደረኝ ድረስ ማንም የውጭ ኃይል ሊከለክል እንደማይችል መዘንጋት የለብንም የጌታን ፈቃድ እንዳንፈፅም እና ይህም ወንጌልን ወደ ዓለም ሁሉ መውሰድን ይጨምራል። ነገር ግ ብዙ ጊዜ የሚከለክለን ድክመታችን፣ ውድቀታችን፣ እምነት ማጣት፣ ኃጥያታችን እና ሌሎች  በልባችን ውስጥ እና በህይወታችን ውስጥ ያሉ የዓለም ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ።

የበለጠ እምነት፣ ፍቅር፣ ለጌታ ሥራ ቅንዓት፣ ድፍረት፣ እና ቁርጠኝነት እንዲኖረን ጌታ ይርዳን። ለእውነት ለመቆም፣ በዕለት ተዕለት ህይወታችን ውስጥ ለመኖር እና ወደ ጠፋው እና እየሞተ ወዳለው ዓለም ለመውሰድ እንድንችል ይርዳን። ምንም ይሁን ምን ለወንጌል እንቅፋት ወይም አሰናካዮች ሆነን አንጨርስ፣ በመጨረሻው ዘመን ውስጥ መሆናችንን አንዘንጋ።

## ጥያቄዎች

1. አንድ ሰው ወንጌልን ማደናቀፍ ይችላል?
2. የክርስቶስን ወንጌል የሚያደናቅፉ እነማን ናቸው?
3. ከእነዚህ አደናቃፊዎች የቤተክርስቲያን አባላት ሊኖሩ ይችላሉ?

4. ለሌሎች ወንጌልን የማንሰብክ ከሆነ ምን ይፈጠራል?
5. በየትኞቹ ሁለት መንገድ ነው ሌሎችን ልናስተምር የምንችለው?
6. በአምልኮ ላይ ሳንገኝ የጌታን ጉዳይ የምንጎዳው እንዴት ነው?
7. ዕብራዊያን 10፡23`27 አንብብና ተወያዩበት
8. በመንፈሳዊ ዲካማ ስንሆን ምን ያስፈልጋል?
9. ክርስቲያን እንዴት ነው መኖር የሚገባው?
10. እንደሚገባን መኖር ሲያቅተን ምን እናድርግ?
11. ቆላስያስ 3፡17 ጥቀስ አንብብ
12. 1ኛ ጴጥሮስ 4፡14~19 አንብብና አብራራቸው
13. ክርስቲያን ማድረግ የሚገቡት ሥራ አላቸው?
14. ያዕቆብ 2 ምን ያስተምራል?
15. መዳናችንን ቸል ብንለው እንዴት እናመልጣለን?
16. እንደሚገባን መስጠት ተስኖን ወንጌልን የምናደናቅፈው በምን መንገድ ነው?
17. መቼ ነው ጌታን የምንዘርፈው? እንዴት ነው ይምንገድበውስ?
18. 1ኛ ቆሮንቶስ 16፡2 ምን ያስተምራል?
19. ከምንም በላይ የክርስቶስን ጉዳይ የሚጎዳ ማን ነው?
20. ጌታ ምን ዓይነት ሰዎች እንድንሆን ይፈልጋል?